
Wisdom at the source of the Blue Nile

ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ

# ናይል

# THE NILE



**እውነትን መፈለግና ለሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!**

2ኛ ዓመት፣ ቁጥር 8 መስከረም 2007 በነጻ የሚታደል

## የዩኒቨርሲቲው ተማሪ ማስታወሻ

በፊታሒ በቃሉ

## የሙርሲ ብሔረሰብ ባህልዊ የአስተዳደር ሥርዓት እና የ“ዶንጋ” ፍልሚያ ጨዋታ

ተመስገን በየነ

## ሶስት ጊዜ

በሂሩት አድማሱ

## Dealing with Sexual Problems & Abnormalities

*Kibrom Mengistu*

## ህልም ለምን እናያለን?

በታምሩ ደለለኝ

## የሀብት ፈጠራ በሬዕይ ጥበብ 2017

በባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)





የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጅነሪንግ እና ሒሳብ ሰልጣኝ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የቤተ ሙከራ ስራዎቻቸውን ለሚስተር ማርክ ጌልፈንድ፣ ለዶ/ር ባይሌ ዳምጤ እንዲሁም ለሌሎች እንግዶች ሲያሳዩ




BDU's community celebrating annual Community Service Day



BDU signing agreement with the University of Aberdeen

**እውነትን መፈለግና ለሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!**

ናይል Nile

በኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት የውስጥ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ክፍል
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

ዋና አዘጋጅ፡-
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

አርታኢዎች
ሞገስ አብርሃ
መስፍን ወዳጆ
ሂሩት አድማሱ

ዘጋቢዎች፡-
አምሳሉ ጥላሁን
ሰሎሞን ብርሃኑ
የማነ ገብሩ
ታድዮ አስማረ
ገበያው ያለው

አምደኞች፡-
ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
ፈታሒ በቃሉ
ፀጋ ጥበቡ

አለባቸው አስፋው

ሂሩት አድማሱ

ታምሩ ደለለኝ
ክብሮም መንግስቱ

ተመስገን በየነ
አረጋዊ ሰለሞን

ግራፊክስና ሌይአውት፡-
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

ፎቶ አንሺዎች፡-
ታምራት አታላይ
ቢንያም አክሊሉ

የኮምፒውተር ጽሁፍ፡-
ፋንታነሽ ላቀው
ታሪክ ታደሰ

ትራንስፖርት፡-
ማናለ ኃይሌ

መልእክተኞች፡-
ቃልኪዳን አወቀ
ንብረት ታፈረ

ስልክ፡- 251 583206088

ኢ-ሜይል፡-internalrelations@bdu.edu.et
or
gracetsegi@gmail.com

ድረገጽ፡- http://www.bdu.edu.et
የፌስቡክ ገፃችን
www.facebook.com/bdu.ethiopia

# አበይት ዜናዎች

## ለሴት መምህራን ስልጠና ተሰጠ

**የማነ ገብሩ**

የዩኒቨርሲቲ የስርዓተ-ፆታ ጽ/ቤት በ2006 ዓ.ም ለቀጠራቸው አዲስ ሴት መምህራን በመማር ማስተማር ዘዴ፣ የፈተና ምዘናና ውጤት አሰጣጥ ላይ ስልጠና ሰጠ፡፡

የተቀጠሩት ሴት መምህራን የመምህርነት ሁለንተናዊ ብቃት ኖሯቸው በራስ መተማመን ላይ የተመሰረተ እውቀት ለተማሪዎች ማስተላለፍ የሚያስችላቸውን የመማር ማስተማር ጥበብ (ፔዳ ጎጅካል ትምህርት) ለተከታታይ 3 ቀናት ወስደዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲ የስርዓተ-ፆታ ጽ/ቤት ዳይሬክተር የሆኑት መምህርት ወ/ሮ ረድኤት መስፍን በስልጠናው መክፈቻ ለሰልጣኞች እንደተናገሩት ዩኒቨርሲቲው በስርዓተ-ፆታ ጽ/ቤት የቀረበለትን ሃሳብ ተቀብሎ በማጽደቅ በዘንድሮው ዓመት ካለፉት ዓመታት በተለየ ሁኔታ ቁጥራቸው በርከት ያሉ ሴት ተማሪዎችን ከየትምህርት ክፍሉ በማስቀረት በመምህርነት መቅጠሩን ተቋሙ ያስቀመጠውን የስርዓተ-ፆታ እኩልነትና ተጠቃሚነት ራዕይ የተወሰነ ነጥብ ወደፊት እየተጓዘ መሆኑን ማሳያ ነው ብለዋል፡፡

በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ያሉት የሴት እና የወንድ መምህራን ቁጥር ለማመጣጠን በተቀመጠው ግብ መሠረት በተቋሙ ውስጥ ተምረው በ2006 ዓ.ም ከተመረቁ ተማሪዎች በየትምህርት ክፍሉ 51 ሴት መምህራን መቀጠራቸው ይታወሳል፡፡ በመጨረሻም የነባር ሴት መምህራን የስኬት ሚስጥርና በህይወት ጉዞአቸውም ያጋጠሟቸውን ችግሮች እና መፍትሄዎችን ልምዳቸውን ለአዲስ ተቀጣሪ መምህራን አካፍለዋል፡፡

## አካዳሚው ሰልጠኞችን አስመረቀ

በታድየ አስማረ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ማሪታይም አካዳሚ ለ6 ወራት ለባህር ምህንድስና በኤሌክትሮ ቴክኒሽያንነት ያሰለጠናቸውን ተማሪዎች ተጋባዥ እንግዶች በተገኙበት በድምቀት አስመረቀ፡፡ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ማተቤ ታፈረ በምረቃ ስነ-ሥርዓቱ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር የኢትዮጵያ ማሪታይም እየሰጠ ያለው ስልጠና የትምህርት ጥራቱን የጠበቀ በመሆኑ ተማሪዎቹ በአለም ገበያ ላይ ተወዳዳሪ በመሆን እየተቀጠሩ ይገኛል፡፡ የማሪታይም አካዳሚ የአስተዳደር ስርዓት መዋቅሩ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ምሳሌ ሆኖ ሊጠቀስ የሚችል መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

ም/ፕሬዚዳንቱ ለተመራቂዎቹ ባስተላለፉት መልዕክት ከሰው ልጅ ባህሪ አንዱ ከራሱ አልፎ ሌሎችን ማገልገል ሲሆን ተመራቂዎች በየትኛውም የዓለም ክፍል ቢሄዱ ቤተሰባችውን፣ ህዝባቸውንና ሀገራቸውን መርሳት እንደሌለባቸው አስገንዝበዋል፡፡ ሀገራችን በኢኮኖሚ አድጋ የተሻለ የኑሮ ደረጃ ላይ እንድትገኝ ድጋፋችሁ ያስፈልጋታል ብለዋል፡፡

በምረቃ ስነ-ስርአቱ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ማሪታይም ማኔጅንግ ዳይሬክተር ሚስተር ጆርዳን ባችለር የማሪታየም አካዳሚ በኢትዮጵያ መከፈት መንግስት እና ዋይ.ሲ.ኤፍ የመርከብ ድርጅት ያስቀመጡትን ራዕይና ግብ መሳካት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ ሚስተር ጆርዳን አክለውም ማሪታይም አካዳሚ ብቁ የባህር መሀንዲሶችን አሰልጥኖ ለአለም ገበያ ማቅረብ ሲሆን ሰልጣኝ ተማሪዎችም በዚህ መስክ መሠማራታቸው የራሳቸው ህይወት ከመቀየር ባሻገር ቤተሰቦቻቸውን እና ሀገራቸውን የሚጠቅሙበት የሥራ መስክ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ተመራቂ ተማሪዎች ምንም እንኳ በሚሄዱበት አካባቢ አዲስና እንግዳ ቢሆኑም የሠለጠኑት ስልጠና በቂ በመሆኑ እንግዳነት ሳይሰማቸው አንደ ልምድ ያለው ኢትዮጵያዊ መርከበኛ ከሥራው ጋር በመቀላቀል እንግዳ እንደማይሆንባቸው አረጋግጠዋል፡፡ ኢትዮጵያን ወክለው የሚሄዱ በመሆኑ የሀገራቸው አምባሳደር መሆን ይጠበቅባቸዋል ብለዋል፡፡ የተመራቂ መኮንን ተወካይ ነጂብ ጀማል እንደገለጸው ተመራቂ መርከበኞችና ቴክኒሽያኖች በሄዱበት ሁሉ ብቃት ያለው ተወዳዳሪ መሆን እንዳለባቸውና በሰለጠኑበት ሙያ ሀገራቸውን ማስጠራት እንዳለባቸው አስገንዝቧል፡፡

በአካዳሚው ገብተው የሚሰለጥኑ ሰልጣኞች የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በመካኒካል እና በኤሌክትሪካል ኢንጅነሪንግ የጨረሱ ናቸው፡፡ ሰልጣኞቹ የባህር ምህንድስናን ለመቀላቀል አካዳሚው የሚሰጠውን የመግቢያ ፈተና በሚገባ የሰሩ እና የሚሰጠውን ስልጠና ለስድስት ወር ተከታትለው በብቃት ሲያጠናቅቁ ነው፡፡ ማሪታይም አካዳሚ በአሁን ወቅት በጣና ሐይቅ ዳር ባታ ቤተክርስቲያን አካባቢ በሚገኘው ግቢ ዘመናዊ ህንፃ በመገንባት እያሰለጠነ ይገኛል፡፡

## ተማሪዎች ስልጠናቸውን አጠናቀቁ

**የማነ ገብሩ**

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከ7-12 ክፍል ደረጃ ለሚገኙ የተውጣጡ ተማሪዎች የሳይንስ፣የቴክኖሎጂ፣የኢንጂነሪንግ እና የሒሳብና እውቀታቸውን ለማሳደግ በክረምት መርሃ ግብር ለ45 ቀናት ስልጠና ሰጠ፡፡

መርሃ ግብሩ በ2004 ዓ.ም የተቀረፀ ሲሆን በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች ጎበዝ ተማሪዎች በመመልመል በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በሒሳብና ኢንጂነሪንግ እውቀታቸው ለማሳደግ በእረፍት ጊዜያቸው የተግባር ተኮር ስልጠና በመስጠት ተስጥኦቸውን ለማሳደግ አልሞ የተቀረፀ ፕሮግራም ነው ያሉት በማዕከሉ አስተባባሪ የሆኑት አቶ ብሬ ጌቴ ናቸው፡፡ እንደ አቶ ብሬ ገለፃ ማዕከሉ በአሜሪካዊ ባለሃብት በሚስተር ማርክ ገልፈንድ የቤተሰብ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ድጋፍ አማካኝነት የተጀመረ ፕሮግራም ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ የራሱ የሳይንስና እና የቴክኖሎጂ ማበልፀግያ ላብራቶሪ ማዕከል ገንብቶ ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ተማሪዎችን ተቀብሎ በተግባር የተደገፈ ስልጠና በክረምት መርሃ ግብር እየሰጠ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ማዕከሉ ከተመሰረተበት 2004 ዓ.ም ጀምሮ ከክልሉና ከቤንሻንጉል ጉምዝ የተለየ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎችን በመመልመል በ3 ተከታታይ አመታት ውስጥ አንድ ሺህ ሶስት መቶ አርባ ተማሪዎች ተቀብሎ በቴክኖሎጂ የተሻለ እውቀት እንዲኖራቸው በማድረግ በተግባር የሚታይ ሥራ እየሰራ ነው፡፡

በስልጠናው ማጠናቀቂያ ዝግጅት ላይ ተማሪዎች በስልጠና ቆይታቸው በተግባር የሠሩአቸውን የፕሮጀክት ውጤቶች አሳይተዋል፡፡ ከሰራቸው ስራዎች መካከል የቤት ውስጥ ሙቀት መቆጣጠሪያ፣ የቤት መብራት መጠን መቆጣጠሪያ፣ የበር መከፈትና መዘጋትን የሚጠቁም ቴክኖሎጂ እና ሌሎች የቴክኖሎጂ ውጤቶችን አቅርበዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ተማሪዎች የእንግሊዘኛ ቋንቋቸውን ለማሳደግ በሁለት ተቃራኒ ቡድን በመሆን Money is better than knowledge or Knowledge is better than money በሚል ርዕስ ጉዳይ ክርክር አካሂደዋል፡፡

# መልዕክቶችና አስተያየቶች

## ርዕሰ-አንቀጽ

## ለላቀ ስኬታማ ጉዞ እንረባረብ!

ያሳለፍነውን 2006 ዓ.ም መልካም ተሞክሮዎች የታዩበት ነበር። ዩኒቨርሲቲያችን በመማር ማስተማር፣ በምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት እንዲሁም በመልካም አስተዳደር የጥራት ዋንጫ ተሸላሚ ነበረ። በዓመቱ ብዙ የምርምር ፕሮጀክቶች ተሰርተዋል፤ አዳዲስ ፕሮጀክቶችም ተጀምረዋል። በመማር ማስተማሩ ደግሞ ከ6600 በላይ የሆኑ ተማሪዎች በአንደኛ፣ በሁለተኛ እና በሶስተኛ ዲግሪ ተመርቀዋል። ከዚህም ጋር በተያያዘ ለቀድሞ የናይጄሪያ ፕሬዝዳንት ኦሊሴጉን ኦባሳንጆ ለአፍሪካ ሰላምና ደህንነት እያደረጉ ባሉት አስተዋፅኦ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሰጥቷል። በትምህርት የልማት ሰራዊት ግንባታ በርካታ መደላድሎች ተፈጥረዋል፣ በየኮሌጆቹ፣ በየኢንስትቲዩቱና በትምህርት ክፍሎች ደረጃም ዓለም አቀፋዊና ሀገር አቀፋዊ ትምህርታዊ ጉባኤዎች ተካሂደዋል፤ ማህበረሰብ ተኮር ችግር ፈቺ የምርምር ስራዎችም ተሰርተዋል። ሌላው አሮጌው ዓመት ዩኒቨርሲቲያችን አዲስ የሰራተኞችን መዋቅር በመጠቀም ምደባ አካሂዷል። በዓመቱ ከጠንካራ ስራዎች ተነሳን እንጂ ውስንነቶች አልነበሩም ማለት አይቻልም። ከተቋም እስከ ግለሰብ ደረጃ በ2006 ዓ.ም የነበረውን አፈጻጸም በመገምገም፣ ጥንካሬያችንን አጎልብተን በመስራትና ውስንነታችንን በማጥበብ 2007 ዓ.ም ስኬታማ የመማር ማስተማር፣ የምርምርና የማህበረሰበ አገልግሎት የሚከወንበት እንዲሆን ለማድረግ ከእያንዳንዱ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ጠንካራ ስራ ይጠበቃል። የተቋሙን ማህበረሰብ ለማነቃቃት በተሰሩ ሥራዎችም ተስፋን የሚፈነጥቁ አዝማሚያዎች ታይተዋል።

በ2007 ዓ.ም ባለፈው ዓመት የተጀመሩ ስራዎችን አጠናክረን በመቀጠል የሀገር ተስፋነታችንን ማረጋገጥ ይጠበቅብናል። ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለመሆን በምናደርገው ያላሰለሰ ጥረት ተጨባጭ የሆኑ ስራዎችን በመስራት ለውጤታማነት መታተር ይኖርብናል። ለዚህም ዩኒቨርሲቲያችን የድህረ ምረቃን መርሃ ግብሮችን ማስፋፋት (የፒ.ኤች.ዲ፣ የማስትሬት ዲግሪ)፣ በቴክኖሎጂ የዕውቀት ሽግግር በማድረግ ሀብትን መፍጠር፣ ችግር ፈቺ የማህበረሰብ አገልግሎት፣ የተሻሻለ የውስጥና የውጭ ተግባቦትና ፖርትነርሺፕ በመገንባት ለርዕይ 2017 ስኬት ጠንክሮ ይሰራል። ርዕይ 2017 የማይደረሰበት ርቆ የተሰቀለ ተስፋ አይደለም። ይልቁንም በትጋት እያንዳንዱ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በተሻለ ፍጥነት ከሰራ ከተቀመጠለት ጊዜ አስቀድሞ ሊያሳካው የሚችለው ግብ እንጂ። በመማር ማስተማሩ ላይ ያለው ሀይል ጠንክሮ ከሰራን፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር በተሳካ መልኩ ማከናወን እና ችግር በሚፈታ የማህበረሰብ አገልግሎት ላይ ትኩረት ካደረግን ተቋሙን እንደራሳችን በማየት የተለያዩ ችግሮች ሲከሰቱ የመፍትሄ አካል በመሆን ከተባበርን ካለምነው እንደምንደርስ አንጠራጠርም። ስለሆነም የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ በተለያየ ክፍል ውስጥ የሚገኘው የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ እያንዳንዱን ነገር ሲያከናውን ለተቀመጠው ርዕይ ስኬት ያለውን አስተዋጽኦ በመመርመር መሆን ይገባዋል።

በተጠና እና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ እያንዳንዱ እንቅስቃሴያችን ከተቃኘ ለዩኒቨርሲቲውም ሆነ ለሃገር እድገት ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል። ሁሉም የድርሻውን በብቃት ከተወጣ ደግሞ ለውጥ ማግኘት ተፈጥሯዊ ነው። ሀገር ማለት እኛ ነን። ስለሆነም በስራ ሂደት ውስጥ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመቅረፍ እልህ አስጨራሽ ትግል እስከመጨረሻው በማድረግ ለሀገራችን፣ ለመጪው ትውልድ የተሻለች ኢትዮጵያን ለማስረከብ መጣር አለብን። አንድ ትልቅ መሪ የተናገረው አባባል እዚህ ላይ መጥቀስ ተገቢ ነው። «ሀገሬ ምን አደረገችልኝ ሳይሆን እኔ ለሀገሬ ምን ሰራሁ?» የሚለውን። ይህን ጥያቄ ራስን መጠየቅና በሀገር ዕድገት ላይ የድርሻን ለመወጣት አቅምን አሟጦ መጠቀም ከአንድ ሀገር ዜጋ የሚጠበቅ ተግባር ነው። ዛሬ ትልልቅ ሆነው ከሀገራቸው አልፈው አለምን በመመምራት ላይ ያሉ ሀገራትን ብንመለከት ይህንን ያህል መግነን የቻሉት ጠንክረው በሚሰሩ እና ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ለትውልድ ቅርስ ትተው ለማለፍ በተጉ ዜጎቻቸው ነው። እኛም ካደጉት ሀገራት ዜጎች ስኬት ልንማር የሚገባን ጠንክሮ መስራትንና ከራስ አልፎ ለትውልድ የሚተርፍን ቅርስ መተው ነው።

ሀገር ሀሳባዊ አይደለችም። ተጨባጭ ናት። ለምሳሌ እኛ የምንሰራበት ዩኒቨርሲቲን እንደሀገር ልንወስደው እንችላለን። ዩኒቨርሲቲያች ብቁ ሰልጣኞችን በማውጣት በሀገር ውስጥ ከሚገኙ፣ በአፍሪካ ካሉ ምርጥ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የሚወዳደርና የሚልቅ ከሆነ ተፈላጊ ይሆናል። የሚያስለጥናቸውም ተማሪዎችም ሆኑ የሚያፈልቃቸው ግኝቶች ትኩረት ሳቢ እና ሀብት ፈጣሪ ይሆናሉ። በዚህም ሀገር የውጭ ምንዛሪ በማግኘት ተጠቃሚ ትሆናለች፤ ዕድገቷም ይፋጠናል። ለዚህ አብነት የባህር ምህንድስና ተቋም ተመራቂዎችን ማየት ይቻላል። በዩኒቨርሲቲያችው የታቀዱ ዕቅዶችን ለማሳካት የቻልነውን ያህል ከተጋን ለውጥ ሩቅ አይደለም። በተሰለፍንበት መስክ ውጤታማ ሆን ማለት ሀገራችን እንድታድግ የድርሻችንን ሰራን ማለት ነው።በመማር ማስተማር ሂደቱ የተሻለ ዕውቀትን በማካፈል፣ በምርምር አዳዲስ ግኝቶችን በማስተዋወቅ ሀብት በመፍጠርና በማህበረሰብ አገልግሎት ከተገኙ መልካም ተሞክሮዎች ማህበረሰባችን ተጠቃሚ በማድረግ ወደ ስኬት የምናደርገውን ጉዞ ማቀላጠፍ ይኖርብናል። ሀገራችን እዚሁ እደጃችን ነው ያለችው። የዩኒቨርሲቲያችን መፃኢ ተስፋ በእያንዳንዳችን ጥረት ላይ የተመሰረተ ነው። ስለሆነም ዛሬን ጠንክረን በመስራት በእያንዳንዱ ቀን ውጤት ማስመዝገብ አለብን።

ዋና ዋና የሆኑ የዩኒርሲቲያችንን ምሰሶዎች መማር ማስተማር፣ ምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት እንዲሁም የተሳለጠ የውስጥና የውጭ ተግባቦትን በማድረግ ቀልጣፋ ስራን ማከናወን ናቸው። የመማር ማስተማር ሂደቱ መምህራንና ተማሪዎች በክፍል ውስጥና በተግባር ትምህርቶች በየዓመቱ አዳዲስ እውቀቶችን በማከል እና ተማሪዎችን ለምርምር ወይም ለፍልስፍና በሚመራ መልኩ የተቃኘ እንዲሆን ያስፈልጋል። በትምህርት ገበታ ላይ የሚቀርበው እውቀት አመለካከትንና አስተያየትን የሚያቃና ለጥናትና ለምርምር የሚጋብዝ መሆን አለበት።

በምርምር ሂደትም ከዚህ ቀደም ሲደረግ እንደነበረው ኑሮን የሚያቃልል፣ ቴክኖሎጂን የሚያስፋፋ እና ሀብት ለመፍጠር የሚረዳ ግኝትን መፍጠር አስፈላጊና አዋጪ ነው። ስለሆነም በዩኒቨርሲቲያችን የሚደረጉ ምርምሮች በተቻለ መጠን የሀገራችንን አውድ ያገናዘቡ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ እና በቀላሉ የሚለመዱ፣ ሀብት ከመፍጠር ረገድ ደግሞ ባለሙያው ለፍቶ የፈጠራ ውጤት ካቀረበ በኋላ ከፈጠራው ሃብት የሚያገኙበት ሥርዓትም ተፈጥሯል። ይህ ሲነገር ከባድ የሚመስል በብርታትና በፅናት ከተገባበት ግን ለውጥ የሚገኝበት የስኬት መስመር ነው።

ችግር ፈቺ የማህበረሰብ አገልግሎት ህብረተሰብን ወደ ተሻለ ህይወት የሚያሸጋግር ነው። በዩኒቨርሲቲያችን ውስጥ የሚገኙ ምሁራን በሙያ መስካቸው የማህበረሰብን የኑሮ ሁኔታ፣ ጤና ፣ አስተሳሰብ፣ ስነ ልቦናዊና ማህበራዊ ትስስር የተሻለ እንዲሆን መጣር ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ረገድ በ2006 ዓ.ም የተሰሩ በሰውና በእንሰሳት ጤና ጥበቃ፣ በጤናማ ምግብ ዝግጅት፣ በትምህርት እና በሌሎችም ዩኒቨርሲቲው በሚገኝበት አካባቢ ለሚኖሩ ማህበረሰቦች አቅም መስጠቱ ለስኬታማ ጉዞው ተስፋ ሰጪ ጅምሮች ናቸው። በቀጣይነት ሌሎችም ማህበረሰቡ ችግር በሚላቸው ርዕሰ ጉዳዩች ሳይንሳዊ መፍትሔዎችን በአፋጣኝ በመስጠት ዩኒቨርሲቲያችን አጋርነቱን ማሳየቱን ይቀጥላል።

2007ዓ.ም ለ2017 ዓ.ም ስኬት አንዱ ግብዓት ነው። ይህ ዓመት የስራ ዓመት የስኬት አመት እንዲሆን የምናደርገው ደግሞ እኛ ጠንክረን ስንሰራ ነው። በእያንዳንዱ ጉዞአችን በአዕምሮዋችን ይዘን የምንቀሳቀሰው የቁጭት ስሜት በአፍሪካ ከሚገኙት አስር ምርጥ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ እኔ የምሰራበት ዩኒቨርሲቲ ለምን አንዱ አይሆንም ብለን ትግላችንን ማፋፋም አለብን። በሃገር ደረጃ ኢትዮጵያ ትልቅነቷን ለመመለስ ትልቅ ግድብ በመስራት እየተጋች እንዳለችው ሁሉ ዩኒቨርሲቲያችን በ2017 ላስቀመጠው ርዕይ ስኬት ጉዞ ጠንክረን እረባረብ!!

## ቁልፍ መልዕክት

### የሀብት ፈጠራ በራዕይ ጥበብ 2017

ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት

የምርምር ዩኒቨርሲቲ አንዱ መገለጫው ለሀብት ፈጠራ ዋነኛ ምንጭ በመሆን ነው። እዚህ ላይ ሀብት ስንል ምን ማለታችን ነው? እንዴት ነው ሀብት የሚፈጠረው? በሀገራችን ያልተለመዱና አዳዲስ የሀብት ምንጮች ምንድን ናቸው? በምን አይነት ሁኔታ በሀገራችን ገብተውና ተላምደው የሀብት ምንጭ ይሆናሉ? ወዘተ. የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳት በዩኒቨርሲቲያችን ማህበረሰብ ልንወያይባቸው ይገባል። በዚህ አጭር ጽሑፍ የምናተኩረው በራዕይ ጥበብ 2017 የሀብት ፈጠራን ለማሳለጥ የተካተቱ ጭብጦችን በመግለጽ ላይ ይሆናል። ስለሆነም የሀብትም ሆነ የሀብት ፈጠራ እይታዎች ከራዕዩ ጋር የተሳሰሩ ናቸው።

በራዕይ ጥበብ 2017 ሀብት ፈጠራ የሚያካትታቸው በሌሎች ሀገሮች ውጤት ያመጡ ቴክኖሎጂዎችን፣ ከመፃህፍና ከተለያዩ ዋቢ ጽሑፎች የተገኙ ሀሳቦችንና ቴክኖሎጂዎች እንዲሁም በራስ ፈጠራ የተገኙ ሀሳቦችንና ቴክኖሎጂዎች በተግባር ላይ በማዋል አዲስ የስራ ዕድልና ሀብት መፍጠርን የያዘ ነው። እዚህ ላይ ግልጽ ሊሆን የሚገባው ጉዳይ ሀብት ፈጠራ በአይን የሚታይና በእጅ የሚጨበጥ ምርት ማምረትን ብቻ የሚጠቃልል ጉዳይ አለመሆኑን ነው። የመልካም አስተዳደር ጉዳዩች ላይ የነበረን ሀሳብ ወይም አዲስ ሀሳብ ፈጥሮ የተሳለጠ መልካም አስተዳደር እንዲመጣ የሠራ ግለሰብ ወይም ተቋም ሀብት ፈጠራ ላይ ሚናው ከፍተኛ ነው። ያለ መልካም አስተዳደር አዳዲስ ሀብት የሚፈጠሩበት አግባብ እጅግ ውስን ነውና ተወዳጅነት ያለው የአማረኛ ልብወለድ የፃፉና በዚሁ ልብ ወለድ ማህበረሰቡ አዳዲስ የሀብት ምንጮች እንዲፈልግ በማመላከት ከፍተኛ የሀብት ፈጠራ መሪ መሆን ይቻላል። ያለችንን ውስን ሀብት በሚገባ የምናስተዳድርበትን አግባብ በመቀመርና ልንተገብረው እንድንችል ሁኔታዎችን በመፍጠር እንዲሁ ይባክን የነበረን ሀብት ማስቀረት ሀብት መፍጠር ነው። በተለያዩ እርከኖች የሚሰጡን ትምህርቶች በሚገባ በመፈተሽ ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ ሀብት ፈጠራ ነው።

ወደ ገጽ 4 ዞሯል ...

**እውነትን መፈለግና ለሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!**

# አበይት ዜናዎች...

## የዩኒቨርስቲው የጤና ባለሙያዎች ሙያዊ አስተዋጽኦ እያደረጉ ነው

በአምሳሉ ጥላሁን

የኢትዮጵያ ቀዶ ህክምና ማህበር 19ኛውን ጠቅላይ ጉባኤ ነሐሴ 2006 ዓ.ም ላይ በባሕር ዳር ከተማ አካሄደ። የማህበሩ ፕሬዚዳንት የሆኑት ዶ/ር ሚላርድ ደርበው ጠቅላላ ጉባኤ በውቢቷ ባሕር ዳር ከተማ እንዲካሄድ የተፈለበት ዓላማ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲንና የአማራ ክልል ጤና ቢሮ ከማህበሩ ጋር ለማስተሳሰር እንደሆነ እና በማህበሩ ውስጥ ሆነው የተሻለ ምርምር፣ ህክምና፣ የማስተማር አገልግሎት /አስተዋጽኦ/ ላደረጉ ሰዎች እውቅና ለመስጠትና ባለፈው የሥራ ዘመን የነበሩትን ጠንካራና ደካማ ጐኖች በመለየት ለሚቀጥለው የሥራ ዘመን እንደግባት ለመቀጠም እንደሆነ ገልፀዋል።

የዕለቱ የክብር እንግዳ የነበሩት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ እንደተናገሩት ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በአሁኑ ወቅት በ8 ግቢዎች ከ45,000 በላይ ተማሪዎችን እያስተማረ እንደሚገኝ እና በ2025 አፍሪካ ውስጥ ካሉ 10 ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ለመሆን የተለያዩ የምርምር ጭብጦችን በመምረጥና የ2ተኛ ዲግሪ ትምህርትን ለማስፋፋት እየሰራ እንደሆነ ተናግረዋል። ዩኒቨርሲቲው በተለይም በጤናው ዘርፍ ትኩረት በመስጠት እየሰራ እንደሚገኝ ገልፀዋል። ስለሆነም የጤና ሳይንስ ኮሌጅም በራሱ አዲስ ግቢ ደረጃቸውን የጠበቁ የቤተ-ሙከራ፣ የመኝታ እና  የማስተማሪያ ክፍሎችን እያስገነባ እንደሚገኝ ገልጸው  ከኢትዩጵያ ቀዶ ሕክምና ማህበር ጋር አብሮ ለመስራት ዩኒቨርሲቲው ፍላጐት እንዳለው አሳውቀዋል።

ከ19ኛው ጠቅላላ ጉባኤ በፊትም በፋኖተ-ሰላም፣ በደብረታቦርና በባሕር ዳር ሆስፒታሎች በመዘዋወር ለአንድ ሳምንት ያህል በነጻ የቀዶ ህክምና አገልግሎት ሰጥቷል።  የኢትዩጵያ ቀዶ ሕክምና ማህበር በአገራችን ውስጥ ባሉ ሆስፒታሎች እየተዘዋወረ ለህሙማን የቀዶ ሕክምና አገልግሎት የሚሰጥ ማህበር ነው። ባለፉት ዓመታትም በብዙ ሺህ ለሚቆጠሩ ህሙማን የቀዶ ሕክምና አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል።

## ዩኒቨርስቲው ስታስቲክስ ትምህርትን ለማሳደግ እየሰራ ነው

በሰለሞን ብርሃኑ

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሳይንስ ኮሌጅ ሥር የሚገኘው ስታቲክስ ት/ክፍል መረጃን በአግባቡ በመያዝና በማደራጀት በተገቢው ቦታና ጊዜ ለሚፈልጉ አካላት በተለይ ለተመራማሪዎች እንዲያገኙ የሚያግዝ ኮንፈረስ አካሄደ።

የሳይንስ ፋኩልቲ ዲን ዶ/ር እሰይ ከበደ የስታስቲክስ ት/ክፍል በ2001 ዓ.ም መጀመሩን አውስተው የት/ክፍል መጀመር ዋና ዓላማ በሀገራችን ያለውን የተበጣጠሰ መረጃ አያያዝን የሚያደራጅና መረጃውን በአግባቡ የሚይዝ ሙሁራንን ማፍራት ነው ብለዋል።

የዩኒቨርሲቲው የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፍራው በበኩላቸው ዩኒቨርሲቲው ሶስት መሰረታዊ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል። እነዚህም መማር ማስተማር፣ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት እና የቴክኖሎጅ ስርጸት መሆናቸውን ጠቅሰው በምርምር ረገድ ግን የዩኒቨርሲቲው ሙሁራን ለሚያካሂዱት ጥናት  የሚፈልጉትን መረጃ ለማግኘት ሲቸገሩ ይታያሉ። ይህን ከመረጃ አያያዝ ጉድለት የሚፈጠር ሲሆን እንደዚህ አይነት መድረኮች መካሄዳቸው ደግሞ ተመራማሪዎችና የስታስቲክስ ባለሞያዎች በመገናኘት በመረጃ አያያዝ ዙሪያ ሀሳብ እንዲለዋወጡ ከፍተኛ እድል ይፈጥራል ብለዋል።

በወቅቱ ከደቡብ አፍሪካ ክዋዙሉ ዩኒቨርሲቲ የመጡ ፕሮፌሰር ተመስገን ዘወትር ጥናታዊ ውጤት ያቀረቡ ሲሆን በጥናታቸውም የስታስቲክስ ጠቀሜታ፣ የሚያስገኘው ውጤት እንዲሁም በሚያጋጥሙ ችግሮች ላይ ያተኮሩ ነጥቦችን አንስተዋል፤ ከዚህ በተጨማሪም በዚሁ ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆኑት ፕሮፌሰር ደሊያኖርዝ የስታስቲክስ ትምህርት በታዳጊ ሀገሮች በሚል ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርበዋል። በኮንፍረንሱ ከኢትዮጵያ ስታስቲክስ ማህበር የቦርድ አባላት፣ ከደቡብ አፍሪካ ከዋዙሉ ዩኒቨርሲቲ፣ ከክልሉ ስታስቲክስ ቢሮ፣ የዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ አመራሮችና ሙሁራን ተገኝተዋል።

በተመሳሳይ ሁኔታ የኢትዮጵያ ስታስቲክስ ማህበር ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ስታስቲክስ ትምህርት ክፍል ጋር በመተባበር ቅርንጫፉን በዩኒቨርሲቲው የከፈተ ሲሆን በጋራ የሚሰሩባቸውን የመግባቢያ ስምምነት የዩኒቨርሲቲው የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራውና የኢትዮጵያ ስታስቲክስ ማህበር ፕሬዚዳንት ዶ/ር ሽብሩ ተመስገን ተፈራርመዋል።

በስምምነቱ ወቅት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው ከማህበሩ ጋር መፈራረማችን የስታስቲክስ ሙያ በማህበረሰብ ሳይንስ፣ በተፈጥሮ ሳይንስና በቴክኖሎጅው ዘርፍ ሁለገብ ስለሆነ በጋራ በመሆን ችግር ፈች የሆኑ ምርምሮችን ለመስራት  ይረዳል ብለዋል። ዶ/ር ተስፋዬ አክለውም ስምምነቱ  የተበጣጠሱ መረጃዎችን በአግባቡ በማደራጀት ችግር ፈች የሆኑ ምርምሮችን እንዲናደርግ ያግዘናል ብለዋል።

የማህበሩ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ሽብሩ ተመስገን በበኩላቸው ማህበሩ በ1982 የተመሰረተ ሲሆን እያከናወናቸው ያሉ ተግባራት ሀገር የሚመራው በመረጃ እስከሆነ ድረስ በሁሉም ዘርፍ ያሉ መረጃዎች ትክክለኛ እንዲሆኑ እና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ መስራት ነው ብለዋል። ዶ/ር ሽብሩ አክለውም መረጃ ለሚሰበስቡ አካላት በተለይ በጤና፣ በኢኮኖሚ፣ በትምህርት የመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ለሚሰሩ ተማሪዎች መረጃን እንዴት መሰብሰብ እንዳለባቸው የማማከር አገልግሎት እንሰጣለን ብለዋል።

## የሀብት ፈጠራ በራዕይ ጥበብ 2017...

ከገጽ 3 የዞረ...

በዩኒቨርሲቲያችን የሚሰጡ ትምህርቶች ሁሉም ለሀብት ፈጠራና ለአጠቃላይ ማህበረሰብ እድገት ሚና ያላቸው ናቸው። ይህን አጠቃላይ የራዕይ ጥበብ 2017 እይታዎች በአጭሩ ካስቀመጥን በኋላ በተጨባጭ ምሁራኖቻችንና ተማሪዎቻችን በሀብት ፈጠራ ሚናቸውን ለማሳደግ እየተሠራ ያለውን ተግባር በአጭሩ እንግለጽ። ዩኒቨርሲቲው “ባህር ዳር የተሠራ (Made in Bahir Dar initiative)” ብሎ በቀረፀው ፕሮግራም አማካኝነት ማንኛውም አዲስ የሀብት ምንጭ የሚሆን ሀሳብ አለኝ ብለው ሀሳብ የሚያቀርቡ መምህራንና ተማሪዎች ያሰቡትን ጉዳይ በተግባር ሠርተው እንዲያሳዩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ላይ ያተኮረ አቅጣጫ አስቀምጧል። ዩኒቨርሲቲው በዚህ ፕሮግራም ሊያሳካ ያሰበው ጉዳይ አዳዲስ የሥራ መስኮች ተከፍተው የስራ ዕድል እንዲበራከት፣ አዲስ የሀብት ምንጭ እንዲኖርና የሀገራችንን ለውጥ በሀገራችን ዜጐች መሪነት እንዲፈፀም በሚደረገው ርብርብ ድርሻውን በሚገባ ለመወጣት ነው። ባለፉት ጥቂት አመታት ለሀብት ፈጠራ በሰጠነው ትኩረት በርካታ ወጣት መምህራኖቻችንና ተማሪዎች አዲስ የሀብት ምንጭ የሚሆኑ ቴክኖሎጂዎችንና አሠራሮችን አቅርበዋል፡፡ የተወሰኑትም አዲስ የሀብት ምንጭ ሆነው የውጭ ምንዛሬ ከማስቀረታቸውም በላይ በሚሊዬን የሚቆጠር አዲስ የሀብት በተጨባጭ አስመዝግበዋል።

ቡና ቤት መክፈትና የመሳሰሉ እጅግ ውስን የሀብትና የሥራ ዕድል ምንጮች ላይ ብቻ ሳንጠለጠል በርካታ ያላየናቸውንና ድንግል የሀብት ምንጮችን በሚገባ እያጠናን ተግባር ላይ በማዋል ለራስም ሆነ ለሀገር አለኝታ የምንሆንበት ጊዜ አሁን ነው። በመሆኑም ምሁራኖቻችንና ተማሪዎቻችን ይህን የራዕይ ጥበብ 2017 አቅጣጫ መሠረት በማድረግ የወደፊቷ ኢትዮጵያን ኩባንያዎች መስራች በመሆን ለራሳችሁ፣ ለቤተሰቦቻችሁና ለሀገራችሁ ብልጽግና ፋና ወጊዎች እንድትሆኑ በጋራ እንስራ። ሀሳባችሁ በተግባር እንዲውል ድጋፋችን አይለያችሁም።

**ራዕይ ጥበብ 2017ን እናሳካለን!**

# አበይት ዜናዎች...

## ምሁራን ለኢኮኖሚ ዕድገቱ ያላቸውን አስተዋፅኦ እንዲቀጥሉበት ተጠየቁ

አምሳሉ ጥላሁን

የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ማህበር እና የባሕር ዳር ቅርንጫፍ 6ኛውን ዓመታዊ ስብሰባ አካሄዱ፡፡ በስብሰባው ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር የተከበሩ አቶ ገዱ አንዳርጋቸው እንደገለጹት የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ማህበር እንዲሁም የባሕር ዳር ቅርንጫፍ በየአመቱ የሚያካሂዳቸው የተለያዩ ስራዎች ለአገሪቱ እንዲሁም ለክልሉ ኢኮኖሚ ዕድገት የራሱ የሆነ አወንታዊ አስተዋጽኦ እያደረገ እንደለ ገልጸዋል፡፡ ይህ የባለሙያዎች ማህበር የአገሪቱንና የክልሉን ፖሊሲ በማውጣት፣ በመተግበር፣ በአቅም ግንባታ እንዲሁም በምርምር ዘርፍ የላቀ አስተዋጽኦ እያደረገ የሚገኝ እንደሆነና በአገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት ላይ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ እያደረገ እንደሚገኝ እና ወደፊትም ይህ ማህበር በምርምር ዘርፍ፣ በአቅም ግንባታ፣ በፖሊሲ ማውጣትና በራሱ ሃሳብ ነጻ ምርምር የሚያስፋፋና የሚያካሂድ እና የተመራማሪዎችን አቅም ወይም ችሎታ የሚያሳድግ መሆን አለበት ሲሉ ገልጸዋል፡፡ ይህ የባለሙያዎች ማህበር እንደመሆኑ መጠን በአገሪቱ እንዲሁም በክልሉ ኢኮኖሚ ላይ የሚታዩትን ችግሮች ነቅሶ በማውጣት የመፍትሄ አካል መሆን እንዳለበትና ለአገር እድገት የራሱን አስተዋጽኦ ማድረግ እንደሚገባው አሳስበዋል፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት የሆኑት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው እንደተናገሩት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በመማር ማስተማር፣ በምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎቶች ላይ አትኩሮት በመስጠት እየሠራ እንደሚገኝና አገሪቱ የምትፈልገውን በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል በብዛትን በጥራት ማፍራት፣ አገራዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ጥናትና ምርምሮች ማድረግ እንዲሁም የማህበረሰብ አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝና በ2017 ዓ.ም በአፍሪካ ከሚገኙ አስር ግንባር ቀደም የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ለመሆን ራዕይ ሰንቆ እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡ በመጨረሻም የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ምሁራን በሙያቸው ማህበር በማቋቋም ለማህበረሰቡም ሆነ ለመንግስት አስተዋጽኦ እያደረጉ እንደሚገኙ እና ዩኒቨርሲቲውም ከጎናቸው በመሆን መሥራት እንደሚፈልግ አሳውቀዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ማህበር ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል የሆኑት ዶ/ር አሰፋ አድማሴ በበኩላቸው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ማህበር ጠንካራ የባለሙያዎች ማህበር እንደሆነ እና ማህበሩ የተለያዩ አገራዊና ክልላዊ ችግሮችን በመለየት የተለያዩ ምርምሮችን በማካሄድ ለችግሮች መፍትሄ አፈላላጊ አካል በመሆን እየሠራ እንደሚገኝና የተለያዩ ወርክሾፕ፣ ሲሚናሮችና ስብሰባዎችን ያካሂዳል፡፡ ከዚህ በፊት የነበሩትን ጠንካራ ጎኖች በማስቀጠል እና ደካማ ጎኖቻችን በማስወገድ ለአገራችን ዕድገት በሙያችን የተቻለንን ያህል አስተዋጽኦ ለማድረግ እየሠራ እንደሚገኝ አሳውቀዋል፡፡

ለአንድ ቀን በተደረገው በዚህ ስብሰባ ላይ በክልሉ ኢኮኖሚ ላይ በሚታዩ ችግሮች ዙሪያ የተሠሩ የምርምር ሥራዎች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡ እንዲሁም በቀጣዩ የሥራ ዘመን እንዴት መሥራት እንዳለባቸው ከታዳሚው ግባዓት በመውሰድ ስብሰባው ተጠናቋል፡፡

## ተቋሙ ሰልጣኞችን አስመረቀ

አምሳሉ ጥላሁን

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የመሬት አስተዳድር ኢንስቲትዩት እና የፌዴራል የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስተር ጽ/ቤት በጋራ በመሆን ከአማራ፣ ትግራይና ደቡብ ክልል ለተውጣጡ 60 ሰልጣኞች የካዳስተር፣ ቅየሳና ካርታ ዝግጅት የሁለት ወር ስልጠና ሰጠ፡፡

በምረቃው ሰዓት ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የመሬት አስተዳድር ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር ዶ/ር ታደሰ አምሳሉ እንደገለጹት ኢንስትትዩቱ ከከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስተር ጽ/ቤት ጋር በመሆን በእውቀት፣ በክህሎትና በአስተሳሰባቸው ብቁ እንዲሆኑ ለማድረግ የራሱን አስተዋጾ እየተወጣ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡ በስልጠናው ያገኙትን ክህሎት በተመደቡበት የሙያ ዘርፍ ሥራቸውን በቀላሉ ለመስራት እንደሚያግዛቸው አሳውቀዋል፡፡ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው ዩኒቨርሲቲው በ2017 ዓ.ም አፍሪካ ውስጥ ካሉ አስር ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ አንዱ ለመሆን እየሠራ እንደሚገኝና የምርምር የትኩረት አቅጣጫዎች መርጦ እየሠራ እንደሚገኝ በድህረ ምረቃ ትምህርት ላይ አትኩሮት በመስጠት እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የከተማና የገጠር የማህበረሰብ አገልግሎት ዩኒቨርሲቲው እየሰጠ እንደሚገኝ፤ እንዲሁም የዕለቱ የክብር እንግዳ የተከበሩ አቶ ደሳለኝ አምባው የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ዴኤታ እንደተናገሩት የሰለጠነ የሰው ሃብትን ከማልማት አንጻር ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የማይተካ ሚና እንዳላቸው ኢንዱስትሪው በጽኑ እንደሚያምንና ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር የከተማ ልማት፣ ቤቶች እና ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪን ለማስተሳሰር ጥረት በማድረግ ላይ እንደሆነ እና የዚህ መግለጫ የሆነው የፌድራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ እና የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የመሬት አስተዳድር እንስቲትዮት ባደረጉት የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት መነሻ ለ120 ሰልጣኞች የከተማ መሬት ይዞታ ማረጋገጥ አቅም ግንባታ የሚሆን የቅየሳ ባለሙያዎች ስልጠና ውል ተገብቶ በመተግበር ላይ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡ አቶ ደሳለኝ አክለው እንደተናገሩት ይህ ስልጠና የፌድራል ሚኒስቴር መስራ ቤቱን፣ የአማራ ክልላዊ መንግስት፣ የኢንዱስትሪ እና የከተማ ልማት ቢሮ፣ የባሕር ዳር ከተማ አስተዳድር እና የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የመሬት አስተዳድር ኢንስቲትዩትን ያቀናጀ በመሆኑ ኢንዱስትሪው ከትምህርት ተቋማት ጋር ተደጋግፎ ለመስራት የሚያስችለውን ፈር የቀደደ ነው ማለት እንደሚያስደፍር እና ይህ ትብብር በመሬት አስተዳድር ዘርፍ በጋራ በመስራት የሚቀጥል እንደሆነና በስልጠናው ሂደት በሁለም ተቋማት በኩል ሊስተካከሉ የሚገባቸው ጉዳዮች ትኩረት ተስጥቶቸው የተሻለ ውጤት በጋራ የምናመጣባቸው ጥረቶች ተጠናክረው መቀጠል እንደሚኖርባቸው አሳውቋል፡፡ እንዲሁም በጋራ በመስራት

ወደ ገጽ 7 ዞሯል ...

## ለሥልጠናው ስኬት ዩኒቨርሲቲው የላቀ አስተዋፅኦ እንደነበረው ተገለፀ

የማነ ገብሩ

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከ1ኛ-3ኛ ዙር 22,356 ሰልጣኞች ተማሪዎች የተሳተፉበት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ስልጠና ተጠናቀቀ፡፡

ተማሪዎች የስትራቴጂክ ፖሊሲዎች ትግበራ ላይ ወሳኝ ኃይል መሆናቸውን ተገንዝበው በአገሪቱ የልማት እንቅስቃሴና ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ላይ ተሳታፊና ተጠቃሚ ለማድረግ አልሞ በተዘጋጀው የ15 የስልጠና ቀናት አስፈላጊውን የስልጠና ግብዓት በማቅረብ ሰልጣኞች በአግባቡ ስልጠናውን ተከታትለው እንዲወጡ ዩኒቨርሲቲው የጎላ ድርሻ እንደነበረው የስልጠናው ተሳታፊዎች ተናገሩ፡፡
ከትምህርት ሚኒስቴር በተሰጠው አገር አቀፍ አቅጣጫ መሠረት ስልጠናው ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ለሰልጣኝ ተማሪዎች የምግብ፣ የመኝታ፣ የትራንስፖርት አገልግሎትና የተማሪዎችን የጤንነት ሁኔታ በቅርብ ሆኖ ከመከታተል በተጨማሪ ደረጃውን የጠበቀ የስልጠና ማዕከላት በማዘጋጀት ዩኒቨርሲቲው የተጣለበትን ኃላፊነት በብቃት መወጣት እንደቻለ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዓመት የስነ-ዜጋና ስነ-ምግባር ትምህርት ክፍል ተማሪና የስልጠናው ተካፋይ የሆነው ተማሪ አያነው ሀሰን ተናግሯል፡፡ ተማሪ አያነው ስለስልጠናው አጠቃላይ ሁኔታ ሲገልፅ መንግስትና ህዝብ ባንድ ላይ ሆነው እያሳዩት ያለው እድገትና ለውጥ ብሎም የኢትዮጵያ የህዳሴ ጉዞና ስትራቴጅካዊ ፖሊሲዎችን አዲሱ ትውልድ በሚገባ እንዲያውቅ ሰፊ ዕድል የፈጠረ ስልጠና እንደሆነ ገልፆ ለህዳሴው ቀጣይነትና ውጤታማነት ባገኘው ግንዛቤ ተጠቅሞ የበኩሉን አስተዋፅኦ እንደሚያደርግ ተናግሯል፡፡

ከሥልጠናው ጎን ለጎን ከ90 በላይ ሰልጣኝ ተማሪዎች የበጎ ፍቃድ የደም ልገሳ አድርገዋል፡፡ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የ5ኛ ዓመት የሲቪል ኢንጅነሪንግ ተማሪ ኢሳያስ ተስፋዬ የበጎ ፍቃድ የደም ለጋሽ ከሆኑት ተመሪዎች አንዱ ነው፡ ፡ ተማሪ ኢሳያስ እንደገለፀው ስልጠናው በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ እንደሚባለው ተማሪዎች በአንድ በኩል ስለአገራቸው ወቅታዊ ሁኔታዎች እና ቀጣይ የህዳሴ ጉዞ ከማስጨበጥ በተጨማሪ በፍላጎት ላይ የተመሠረተ የደም ልገሳ በማድረግ የእናቶችና የህፃናትን ህይወት በማትረፍ ዙሪያ ደም በመለገስ የዜግነት ግዴታቸው የተወጡበት ስልጠና እንደነበረ ገልጿል፡፡

**እውነትን መፈለግና ለሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!**

# የዩኒቨርሲቲው ተማሪ ማስታወሻ

(ከባለፈው ዕትም የቀጠለ)

በፈታሒ በቃሉ

ተማሪ ተስፋሁን የሕክምና ትምህርትቱን እንደጀመረ በተረጋጋ አዕምሮ በመከታተል እጅግ በጣም አጥጋቢ ውጤት በማስመዝገብ የመምህራንን ቀልብ ከመሰቡም ባሻገር አብረውት በሚማሩት ተማሪዎችም ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ተማሪ እንደነበርና ከጥቂት ቀናት ወዲህ ግን ባልልጠበቀውና ባላሰበውአጋጣሚ፤ እዝነ ልቦናው ወደ ተለያየ መንገድ እየሸፈተ እንዳስቸገረው፤ በዚህም የተነሣ ሁል ጊዜ ክፍል እየገባ መማር እያስጠላው ስለመጣ አልፎ አልፎ ወደ መሐል ከተማ ወጣ፣ ወጣ ማለት በማዘውተሩ ይባስ ብሎ በኪስ አውላቂ ሌቦች ያለ የሌለ ገንዘቡንና መታወቂያ ካርዱን በመሠረቁ ችግር ላይ እንደሆነ፣ ካሁን በፊት በወጡት ተከታታይ መጣጥፎች እየተገነዘብን መጠናል። አሁንስ ምን ይገጥመው ይሆን........ ለሁሉም አብረን እንከታተል............

## ሣጅንና የግቢ ፖሊሶች

ባለፈው አንተ ችግርህ ምንድን ነው? ብለህ በጠየቅኸኝ ሰሞን ቀደም ብሎ መታወቂያየ ጠፍቶኝ እያለ አንዲት የዚህ ግቢ ተማሪ የሆነች አግኝታ እንደሰጠችኝ ነግሬህ ነበር። ታዲያ ይህች ልጅ መታወቂያዬን ከሰጠችኝ ጊዜ ጀምሮ የሆነ ነገር አብራ የሰጠችኝ ይመስለኛል። አልሁና ዝም ስል.... ሲያዳምጠኝ ቆየና እንዴት? ማለት አልገባኝም አለና መልሶ ጠየቀኝ። የነበረውን ሁኔታ በዝርዝር አስረዳሁትና ይሄውና ዛሬ እሷን ፍለጋ በሄድሁበት ይህ ነገር ተከሰተ ስለው። በጣም አዘነና ታዲያ እኔ ስጠይቅህ ለምን ደበቅኸኝ? አለና ጠየቀኝ። እኔማ አንተ ሳትሰማ ችግሩን ለማቃለል በማሰብ ነው አልሁት። እሱም ይገርማል! እኔ እኮ ከሁኔታህ ብዙ ነገሮችን ተገንዝቤ ስጠይቅህ ሌላ ጊዜ በሰፊው እነግርሃለሁ በማለት ስትሸነግለኝ ላለማጨናነቅ ስል መልሼ ተውሁት፤ አለና በቃ አሁን የሆነው ሆኗል በተቻለ መጠን አዕምሮህን አንድ ካደረግህ ሁሉ ነገር ቀስ በቀስ ይስተካከላል አለኝ። እኔም አይመስለኝም አሁንስ ተስፋ እየቆረጥሁ ነው። ምክንያቱም በዚች ልጅ የተነሣ ገና ብዙ መሰናክል ሳይገጥመኝ አይቀርም። በማለት ስሜት ውስጥ መግባቴን ሲያይ አይዞህ እንደዚህማ በቀላሉ ተስፋ መቁረጥ የለብህም። የሰው ልጅ በዚች ምድር ላይ ሲኖር ብዙ ፈተናዎች ሊገጥመው እንደሚችል አስቀድመህ ማወቅ አለብህ። ደግሞ እኮ ሕይወት ትርጉም የሚኖረው በተለያዩ ፈተናዎች ሲታጀብ ነው። እና አሁን አንተን እንደዚህ እንድትል ያስገደደህ የመታወቂያህ፣ የምግብ ካርድህና የብርህ መጥፋት ነው ወይንስ ልጅቷን በፈለግኸው ፍጥነት አግኝተህ የፍቅር ጥማትህን ማርካት አለመቻልህ? በማለት ጠየቀና አማራጭ መልሶችን ከዘረዘረ በኋላ፤ ለመሆኑ ልጅቷ የምን ተማሪ ናት? አለኝ።

እኔም በአካል ያገኜኋት እኮ ከመጀመሪያው ቀን ጋር ለሦስት ያህል ጊዜ ነው ለዚያውም በድንገት እንደጉም ትታየኝና ወዲያው ትጠፋኛለች በማለት በዝርዝር ነገርሁትና ይህንን ያቀረበልኝን ጥያቄ ለማወቅ ጊዜ እንዳላገኘሁስነግረው በቃ ተወው ችግር የለም ስልኳን ካወቅኸው ቀላል ነው። አለና ራት ለመብላት ወደምግብ አዳራሽ ሄድንና ተሰልፈን። ሰልፍ ይዘን በመንቀሳቀስከቲከሩ ዘንድ ስንደርስ ሣጅን፣ እኔን እያመለከተ ዛሬ በአጋጣሚ በሌቦች ሲሰረቅ ከመታወቂያው ጋር የምግብ ካርዱም አብሮ ስለተሰረቀ ለዛሬን ፍቀድለትና ገብቶ እንዲበላ ይሁን አለው።

*የጥበቃ ሠራተኛና ተማሪ የሚተያዩት እንደ አይጥና ድመት ነው። ነገር ግን አንተ ልፋታቸውን ግንዛቤ ውስጥ ስታስገባላቸው ደስ እንደሚላቸው ምንም ጥርጥር የለውም። ለዚህ ነው እኔም በደካማ ጎናቸው የገባሁባቸው አለና ይስቅ ጀመር፤ እኔም አብሬ ሣቀሁ።*

ቲከሩም

ሸቅብ ቁልቁል ሲያየኝ ቆየና ጊዚያዊ የመመገቢያ ወረቀት ከምግብ ቤት ኃላፊው ጠይቃችሁ ካላመጣችሁ አይቻልም፤ አለና ድርቅ አለብን። ሣጅን ለማግባባት ሞከረ። እሱ ግን እሽ ብሎ ሊያስገባኝ አልቻለም። እኔም በቃ ተወው አንተ ግባና ብላ እኔ እሄዳለሁ በማለት ወደኋላ ስመለስ፣ ሣጅንም አብሮኝ መጣና ለዚህ... ነፍስ አውል ምግባቸው ደግሞ ሲለመኑ አያፍሩም? እንዴ! ደግሞ እኮ ትቢታቸው አያድርስ ነው።አሁን ማን ይሙት የቢፌ ግብዣ ያዘጋጁ አይመስሉም? አለና ከግቢ ውጭ ገዝተን እንበላለን አለኝ።

ወዲያው መታወቂያ ስለሌለኝ መግባትና መውጣት እንደማልችል ስነግረው፣ችግር የለም እኔ እነግራቸዋለሁ አለና በር ላይ ከጥበቃ ሠራተኞች አጠገብ ስንደርስ፤ ሣጅን ትህትና በተሞላበት ሁኔታ ሞቅ ያለ ሠላምታ አቀረበና ሥራ እንዴት ነው? መቼም የተማሪ ነገር እኮ አስቸጋሪ ነው። አንዳንዱ አምሽቶ ይመጣና ይረብሻል፣ ሌላው ደግሞአጥር ሰብሮ ለመግባት ይሞክራል። ብቻ ችግሩ ብዙ ነው። አለና ብሶታቸውን ሲናገር አጀንዳው ከተከፈተስ አሉ መሰለኝ ተማሪው የሚያደርስባቸውን በደል አንድ ባንድ በመዘርዘር ሲያወሩ ቆዩና፣ በመቀጠልም ከመካከላቸው አንደኛው የጥበቃ ሠራተኛ፡- በጣም ይገርማችኋል መቼም ተማሪ ሲባሉ የሚሠሩትን አያውቁም፣ በተለይ መስከረም አካባቢ ከእረፍት ሲመለሱ ከወላጆቻቸው ይዘውትየሚመጡት ገንዘብ እስከሚያልቅ ድረስ መውጣት፣ መጠጣት፣ መዝናናት ያበዛሉ። እናምአንድጊዜ ሦስት ሆነው እስከ ምሽቱ ስድስት ሰዓት ሲጠጡ አምሽተው ሞቅ ብሏቸው መጡና ክፈቱልን እንግባ ሲሉ መታወቂያ አስይዙና ግቡ ስንላቸው አናስይዝም።እንዲሁ መታወቂያ ሳናስይዝ እንግባ በማለት ቁመው መጨቃጨቅ ሲጀምሩ፣ እኛም እንደማይቻል ስንነግራቸው፣ አንደኛው ስማ አንተ፤ ሁሉ ነገር ይቀየራል ይህ የምታየው ሕንፃ እንኳን ቀለም ተቀብቶ ተቀይሯል። አንተ ግን አምናም እንዲሁ ነበርህ አሁንም ያው ሣትቀየር እንዲሁ አለህ። በማለት አሳቀለን። ከዚያ በኋላ ተከታትለን ከሰስነው። ከዚያም ተከስሶከዲሲፕሊን ኮሚቴዎች ፊት ቀርቦ ሲጠየቅአዎ ልክ ነው። ሕንፃው ቀለም ተቀብቶ ተቀይሮ ቆየኝ። እሱ ግን ያው ምንም አልተቀየረም፤ካለ በኋላ በመቀጠል ታዲያ! እንዲህ መባሉ ከመብቱ ጋር ምን ያገናኘዋል? በማለት ሳይፈራ ሣይቸር ለዲሲፕሊን ኮሚቴዎች ተናገረ። የኮሚቴ አባላትምጉዳዩን በመመርመር ነገሩን ቀለል አድርገው በማየት ማስጠንቀቂያ ተ ሰ ጠ ው ። በ ማ ለ ት አ ወ ራ ን ። ሣ ጅ ን ም ል ክ ነው ብዙ እንደምናስቸግራችሁ ይገባኛል። ብቻ እናንተ ትዕግስታችሁ ያስገርማል እያለ ሲያደንቃቸው፣ ምን እናድርግ እኛማ መቸስ ሥራችን አይደል። ካለ በኋላ ብቻ የተወሰኑት ደግሞ ጥሩዎች አሉ። እና በእነሱ ደግሞ እንፅናናለን አለን። ሣጅን በጥሞና ሲያዳምጣቸው ቆዬናለስለስ ባለ አንደበት የእኔ መታወቂያና የምግብ ካርድ በሌባ መሰረቁን በመንገርለእራት መውጣት እንደምንፈልግ ጠየቀናቶሎ እንደምንመለስ ሲያስረዳቸው፣ ችግር የለም፤ አሉን።

ካስፈቀድን በኋላ ከግቢ በመውጣት እያወራን በመጓዝ፣ቦዔዝ ጋርደን ከተባለው ምግብ ቤት ገባንና ሣጅን ሁለት ምግብ አዘዘ። ምግቡ እስከሚመጣአንዱን፣ አንዱን እያወራን ቆየንና ምግቡ ሲመጣ አንድ ኮካኮላ ከአምቦ ውኃ ጋር እንዲመጣልን በድጋሚ አዘዘ። የበላነው ራት በጣም ቆንጆ ነው።ራት ከበላን በኋላ እጃችንን እየታጠብን እያለን፣እዚያ እነሱን ከምንለማመጥ እንደዚህ አይሻልም አለና የተጠቀምንበትን ሂሳብከፈለ።

መቼም ለእኔ ብለህ ብዙ ተቸገርህ፣ በማለት ምስጋናዬን ሳቀርብለት፤ ወይ አንተ! የተጠቀምነው እኮ በጋራ ነው እናም አስቸገርሁት የሚለው አባባል አይሠራም፤ ይልቅስ አሁን አሳሳቢው ነገር መታወቂያህንና የምግብ ካርድህን እንዴት እንደምናወጣው ነው። ስለዚህ ነገ ጠዋት የመጀመሪያ ሥራህ ይህ መሆን አለበት አለኝ። እኔም ልክ ነህ፤ ነገ ክላስም ቢሆን ቀርቼ ክሊራንስ ማስፈረም አለብኝ፤ በማለት አረጋገጥሁለት።

ሣጅን ገንዘብ አይቸግረውም እንደነገረኝ ከሆነ ከመከላከያ ሠራዊት በቦርድ ሲሰናበት በክፍለ ጦሩ የነበሩ አባላት አወጣጥተው ከሰጡት ሃያ ሺህ ብር ላይእሱ በየጊዜው የቆጠበውን አምስት ሺህ ብር በመጨመር ከሃያ አምስት ሽህ ብር ያላነሰ በባንክ ያስቀመጠው ገንዘብ አለው። እንደገና በየወሩ ሦስት መቶ ብር ያህል የጡረታ አበል ያገኛል።።ይሁን እንጅ ያን ያህል ገንዘብ አለኝ ብሎ አይኩራራም ሁሌም የሚመገበው እንደማንኛውም ተማሪ፣ በተማሪዎች ካፌ ነው። ዛሬ ግን ለእኔ ሲል ከግቢ ውጭ መመገብ የግድ ሆኗል። ደግሞ ሣጅን ለገንዘብ ብዙም ስግብግብ አይደለም። ብዙ ጊዜ በቡድን ሥራ ገንዘብ የሚያስወጣ ነገር ካለ ማንንም ሣይጠይቅ አሟልቶ የሚያቀርብ እሱ ነው። አሁንማ ነገሩ እየተለመደ ስለመጣ ይህንን ባያደርግ ተጠያቂ እንደሚሆን አድርገን እየወሰድነው ያለን አንታጣም።

ከምግብ ቤቱ ስንወጣ፣ስለእኔ ጉዳይ እያወራንና ሌላ ሌላውን በመተው ትምህርቴን በደንብ እንድከታተል እየመከረኝ ከጥበቃዎች ዘንድ ደረስን። እዚያ እንደደረስን፣ ጎበዝ እንዴት ናቸሁ? መጥተናል አላቸውናእነሱም አጠፌታውን መልሰውልን፣ሌላው ተማሪ መታወቂያ እያሣዬና እየተፈተሸ ሲገባ እኛ ግን ያለምንም ጥያቄ ዘው ብለን ገባን።

እኔም ነገሩ ገርሞኝ እንዴት ነው? እንደዚች ዓይነቷን ነገር የምትችልባት? በማለት ስጠይቀው፤ ምን መሰለህ የሰው ልጆችን የሥራ ባህሪ ምን ጊዜም ማወቅ አለብህ። ከዚህም አኳያ አንዳንዱ አክብሩኝ፣ አንዳንዱ ፍሩኝ፣አንዳንዱ አሞግሱኝ፣ ሌላው ደግሞ ሥራዬን ዕወቁልኝ ወ.ዘ.ተ...... ይላል። እና ምን እንደሚፈልግካወቅህ፣በደካማ ጎኑ ትገባና እንደፍላጎቱ ታደርጋለህ። ከዚያም ልቦናው መራራት ይጀምራል። እንደምታያቸው እነዚህ የጥበቃ ሠራተኞች ምስኪኖች ናቸው። ተማሪዎች ደግሞ ከዕድሜያቸውአኳያ ማናለብኝ የሚሉበት ዘመን ስለሆነ የእነሱን ተግባርና ኃላፊነት እንደሥራ እንደማይቆጥሩት ግንዛቤ አላቸው።

በዚህም የተነሣ የጥበቃ ሠራተኛና ተማሪ የሚተያዩት እንደ አይጥና ድመት ነው። ነገር ግን አንተ ልፋታቸውን ግንዛቤ ውስጥ ስታስገባላቸው ደስ እንደሚላቸው ምንም ጥርጥር የለውም። ለዚህ ነው እኔም በደካማ ጎናቸው የገባሁባቸው አለና ይስቅ ጀመር፤ እኔም አብሬ ሣቀሁ።ደግሞ እኮ ወታደር እንደነበርሁ አትዘንጋ።

ወታደር በምንም ይሁን በምን ሽንፈትን አይወድም ጠላትን ድል ለማድረግ በመጀመሪያ ያለምንም ወጪ በብልሃት ለማሸነፍ የኢንተለጀንስ ሥራ ይሠራል። ይህ ካላዋጣበትክክለኛው መንገድ ተዋግቶለማሸነፍ ምሽግ ቆፍሮ ተገን ይዞ ጥቃቱን ይቀጥላል። የሆነው ሆኖ እሽ ባይሉም እንወጣ ነበር፤ ሲለኝ እንዴት? አድርገን በማለት ስጠይቀው፤ ምን መሰለህ የጠፋንን ንብረት ፖሊስ ጣቢያ ለማስመዝገብ ስለምንፈልግ ብለን እንወጣ ነበር፤ አለኝና እያወራን መኝታ ቤት ደረስን።

ምኝታ ቤት እንደገባን የደረሰብኝን ዝርፊያ የሰሙ የዶርሜ ልጆች ሁኔታው አሳስቧቸው ሲጠይቁኝና ሲያበረታቱኝ

ወደ ገጽ 11 ዞሯል






Mr. Mark Gelfand, American Philanthropist, addressing BDU community on STEM Incubation Center inaugural function at Dilchibo School, Bahir Dar, Ethiopia

## ተቋሙ ስልጣኞችን...

ከገጽ 5 የዞረ...

ያላቸውን ቁርጠኝነት ለማሳየት ይህን ውጤት እየተከታተለ በመደገፉ የሚሠራ የጋራ ቡድን በቴክኒክ ጉዳዮች እና በከፍተኛ አመራሮች ደረጃ የተደራጀ በመሆኑ ተቀራርቦ በመስራት ውጤት ማስመዝገብ እንደሚቻልም የክብር እንግዳው ገልጸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በመሬት አስተዳድር ኢንዱስትሪ ያለ አስፈጻሚዎች እና ፈጻሚዎች ሁሉ በአገራችን የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባ ገና መሠረት እየተጣለለት በመሆኑና ለመሬት መረጃ አያያዝ ያለን ተሞክሮ ብዙ መሠረታዊ ለውጥ የሚፈልግ በመሆኑ፤ አስቀድሞ የመሬት መረጃን በጥራት የመሰብሰብ እና ተናባቢ የመረጃ ስርዓት መገንባት ላይ ትኩረት ሊሰጥ እንደሚገባና ለዚህ መሰረታዊ የመረጃ አቅም ግንባታ ትልቁን ድርሻ የሚወስደው ስራውን የሚያንቀሳቅሰው የሰው ሃብት በመሆኑ በኢንዱስትሪው የሚሰማራው ሰው ብቃቱ ተረጋግጦ ወደ ሥራ እንዲሰማራ አገራዊ አቋም ተይዞ እየተሰራ እንደሚገኝና ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት ተመራቂዎች ጨምሮ ራስን ለማብቃት የሚያደርጉትን ጥረት አጠናክረው እንደሚቀጥሉ አሳውቀዋል፡
፡

## ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን

የናይል ጋዜጣን ተነባቢነት ለማሳደግ የዝግጅት ክፍሉ የተለያዩ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡ እርስዎም አስተማሪ እና አዝናኝ የሆኑ

- የተለያዩ ጹህፎች
- ማህበራዊ ሳይንሳዊ ኢኮኖሚያዊ እና ቴክኖሎጂ ነክ ጉዳዮች
- የካርቱን ስእሎች
- ቀልድ
- ግጥም

እና የመሳሰሉትን አዲሱ ጥበብ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር G5-02E በሚገኘው ቢሯችን ድረስ በመምጣት ወይም በኢሜል gracetsegi@gmail.com ይላኩልን፡፡

በናይል ጋዜጣ በቀጣይም ለእናንተ ይመጥናሉ ያልናቸውን የተለያዩ ጽሁፎች ማቅረብ እንደምንቀጥል እየገለጽን ለቀጣዩ ጥቅምት ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ በአድራሻችን መላክ ወይም በኢሜል አታች ማድረግ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

ዝግጅት ክፍሉ

እውነትን መፈለግና ለሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!

# ባህላችን

## የሙርሲ ብሔረሰብ ባህልዊ የአስተዳደር ሥርዓት እና የ“ዶንጋ” ፍልሚያ ጨዋታ

ተመስገን በየነ

የፎክሎር (የባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል መምህር

E-mail:- folklorecultureebdu@gmail.com

ውድ አንባቢያን ወደ ዕለቱ ርእሰ ጉዳይ በቀጥታ ከመግባታችሁ በፊት ስለሙርሲ ብሔረሰብ ማኅበር-አካባቢያዊ ዳራ (Socio-Geographical Background) ጥቂምታ የቀረበ መሆኑን በአክብሮት እገልፃለሁ፡፡ መልካም ንባብ!

### 1. ማኅበረ-አካባቢያዊ ዳራ

በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ውስጥ ከሚገኙ የዞን አስተዳደር መካከል አንዱ ደቡብ ኦሞ ነው፡፡ በደቡብ ኦሞ ዞን 16 (አስራ ስድስት) ብሔረሰቦች በአንድ አካባቢ ተሰባስበውና ተሰባጥረው ይኖራሉ፡፡ እነርሱም ሙርሲ፣ ሙርሌ፣ ማሌ፣ ሐመር፣ በና፣ ባጫ፣ ብራይሌ፣ ቦዲ፣ ኛንጋቶም፣ አሪ፣ አርቦሬ፣ ኩዌጉ፣ ካራ፣ ዲሜ፣ ዳሰነች እና ፀማይ ናቸው፡፡ የብሔረሰቦቹ አበይት የኢኮኖሚ መሰረት/ምጣኔ ሃብት አርብቶ አደር፣ ከፊል አርሶ አደር እና አርሶ አደር ሲሆኑ በ1999 ዓ.ም በተካሄደ የህዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት መሰረት የዞኑ ህዝብ ብዛት 577,673 (አምስት መቶ ሰባ ሰባት ሺ ስድስት መቶ ሰባ ሶስት) እንደሆነ ተጠቁሟል፡፡ ከነዚህ ብሔረሰቦች መካከል የሙርሲ ብሔረሰብን ባህልዊ የአስተዳደር ሥርዓት እና የ“ዶንጋ” ፍልሚያ ጨዋታን እንቃኛለን፡፡

የሙርሲ ብሔረሰብ በደቡብ ኦሞ ዞን በሰላማንጎ እና በሎጎፋ ወረዳ የሚኖሩ ናቸው፡፡ መተዳደሪያቸው አርብቶ አደርና ከፊል አርሶ አደር ሲሆኑ የብሔረሰቡ መግባቢያ ቋንቋ “ሙርስኛ” ይባላል፡፡ የሙርስኛ ቋንቋ ከናይሎ ሰሃራዊ ቤተሰብ የሚመደብ ሲሆን የብሔረሰቡ ህዝብ ብዛት 7,500 (ሰባት ሺ አምስት መቶ) እንደሆነ በ1999 ዓ.ም የተካሄደው የህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ ያመለክታል፡፡ ብሔረሰቡ “ኩታመ” እና “ሻቃ” በሚባሉ ሁለት አበይት ጎሳዎች ይተዳደራል፡፡ በሁለቱ አበይት ጎሳዎች ስር አስራ አራት ንዑሳን ጉሳዎች ይገኛሉ፡፡

### 1.1 ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓት

የሙርሲ ብሔረሰብ ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓት በአራት የስልጣን መዋቅርና ተዋረድ የተደራጀ ነው፡፡ የብሔረሰቡ የስልጣን መዋቅርና ተዋረድ “ኩሙሩ፣ ኮይሴ፣ ሂርሃቶ እና ካሚስ” በሚባሉ አመራሮች የተደራጀው ነው፡፡ እነዚህ አመራሮች እንደየደረጃቸው በብሔረሰቡ የተገደበ እና የተወሰነ የስልጣንና የስራ ድርሻ አላቸው፡፡ እያንዳንዱ አስተዳዳሪ ከሚሰራው አለማዊ እና መንፈሳዊ ስራና ተግባር (Secular and Spiritual Function) በተጨማሪ ተጠሪነቱ ለ“ኩሙሩ“ /ንጉሱ/ ነው፡፡ የብሔረሰቡ ባህላዊ የስልጣን ሽግግር በዘር ወይም በጎሳ የሚተላለፍ ሥርዓት ነው፡፡ የብሔረሰቡ መሪ ኩሙሩ/ንጉሱ ሲያርፍ ስልጣኑ ለተከታይ ወንድም (ቅድሚያ ይሰጣል) ወይም ቤተዘመድ እጩዎች በውድድርና በምርጫ ስልጣን ይሰጣል፡፡ የስልጣን ውድድሩ መጀመሪያ ለኩሙሩ /ለንጉሱ/ ወንድሞች፣ ወንድም ከሌሉት ለቅርብ ቤተዘመድ ስልጣኑ ይተላለፋል፡፡ የስልጣን ሽግግር ሥርዓቱ የሚፀድቀው የአገር ሽማግሌዎች፣ አመራሮችና የብሔረሰቡ አባወራዎች ስለወራሹ ጀግንነት፣ ንቃት፣ ጉብዝና፣ የአስተዳደር ብቃትና ችሎታ አስተያየት ከሰጡ በኋላ ነው፡፡ ወራሹ እነዚህን ብቃትና ችሎታዎች የማያሟላ እጩ ከሆነ ለስልጣን እንዳይበቃ የማድረግ ስልጣን አላቸው፡፡

የሙርሲ ብሔረሰብ ባህልዊ አስተዳደር “በኩሙሩ፣ በኮይሴ፣ በሂርሃቶ እና በካሚስ” ሥርዓት እንደሚመሩ ከዚህ በላይ ተጠቁሟል፡፡ የብሔረሰቡ አስተዳዳሪዎች የስራ ድርሻና ሃላፊነት እንደሚከተለው በቅደም ተከተል ቀርቧል፡-

ኩሙሩ (ንጉሱ)፡- የብሔረሰቡ የበላይ አስተዳዳሪ፣ ተቆጣጣሪ፣ ተጠሪ፤ አለማዊና መንፈሳዊ (Secular and Spiritual) መሪ ነው፡፡ የህዝቡን ችግርና አቤቱታ ለኩሙሩ /ንጉሱ/ የሚያቀርቡ ሥርዓት አስፈፃሚ የአገር ሽማግሌዎች አሉ፡፡ ንጉሱም ከሃገር ሽማግሌዎች የቀረበውን አቤቱታ በመቀበል በሬ፣ ላም ወይም ፍየል አርዶ አንጀት በማንበብና በማየት ዝናብ እንዲዘንብ፣ ወረርሽኝ እንዲጠፋ፣ ብሔረሰቡ በሰላም፣ በደስታና በጤና እንዲኖር “ቱም”ን /ፈጣሪውን/ ይለምናል፤ይማፀናል፡፡

ኮይሴ፡- የኩሙሩ /የንጉሱ/ አማካሪና ጉዳይ አስፈፃሚ በመሆን ያገለግላል፡፡ ኮይሴ በአካባቢው ከሚገኝ ልዩና ከተመረጠ የአፈር አይነት ጭቃ አዘጋጅቶ የብሔረሰቡን ታማሚ ሰዎች ሰውነት ጭቃ ይቀባል፡፡ ከዚህ ሥርዓት ጋር በተያያዘ ምራቁን በታማሚዎች ግንባርና ሰውነት ላይ እንትፍ! እንትፍ!... በማለት ከህመማቸው፣ ከስቃያቸውና ከበሽታቸው እንዲፈወሱ ባህላዊ የአምልኮ ሥርዓት ይፈፅማል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አዲስ የእርሻ መሬት ወይም እዳሪ ሲወጣ /ሲታረስ/ መሬቱ እንዲባረክ፣ ሰብሉ እንዲፋፋ፣ ፍሬ እንዲያፈራ እና አዝመራ እንዲይዝ ፍየል አርዶ ደሙን በሚታረሰው ቦታ ላይ በማፍሰስ እና መሰል ባህልዊ ሥርዓትን በመፈፀም ምድሩን ይባርካል፡፡

ሂርሃቶ፡- ህልም አላሚና ትንቢት ተናጋሪ መንፈሳዊ መሪ ነው፡፡ ስለብሔረሰቡ የኑሮ ሁኔታ፣ መጪው ዘመን ጥጋብና ርሃብ ስለመሆኑ፣ የሰላም፣ የጤና፣ የልምላሜ ዓመት በአንፃሩ ደግሞ የግጭት፣ የመከራ፣ የወረርሽኝና የበሽታ ዓመት ሊሆን እንደሚችል ትንቢት ይናገራል፡፡ ለትንበያ የሚቀርቡ ህልሞች ከራሱ እና በስልጣን ከሱ በታች ከሆነው ከ“ካሚሲ” የሚመጡ ህልሞችንና ሃሳቦችን ይቀበላል፡፡ የታዩና የታለሙ ህልሞችን ለመፍታት ባህላዊ ሥርዓት እንዲዘጋጅ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡ በተዘጋጀው ሥርዓት የታለሙ ህልሞች (ህልም በመፍታት በተካነው/ኑ ሂርሃቶ/ዎች) ቀርበው ባህላዊና መንፈሳዊ ፍቺ እና ትንታኔ ይሰጣቸዋል፡፡ በትንቢቱ መሰረት የሚደረጉ ሥርዓቶች እንዲፈፀሙ መመሪያ ይሰጣል፤ የትንቢቱን ትግበራ ሥርዓት ሂደት ይከታተላል፡፡



ፎቶ.ቁ1፡-የሙርሲ ብሔረሰብ ሴቶች ገፅታ (ምንጭ፡-http://www.google.com.et)

ካሚሲ፡- የካሚሲ የስራ ድርሻ ቡና ማፍላት እና መንፈሳዊ ሥርዓትን መፈፀም ነው፡፡ መንፈሳዊ ሥርዓቱን ሲፈፅም የብሔረሰቡን አባላት ነጭ ጭቃ ቀብቶ ይባርካል፡፡ ብሔረሰቡን ከፈጣሪ ጋር ያማልዳል፣ ተብሎ ይታመናል፡፡ ከመንፈሳዊ ተግባራቱ በተጨማሪ ብሔረሰቡን ከበላይ አስተዳዳሪ አካላት ያገናኛል፡፡ በአጠቃላይ የአስተዳደር ሥርዓታቸው ከአለማዊ ይልቅ መንፈሳዊ ተግባራት ላይ ያመዝናል፡፡

የሙርሲ ብሔረሰብ፤ ከአካባቢው (በጎሳ፣ በቤተሰብና በግለሰብ) እና ከአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር ለሚከሰቱ ግጭቶች እርቅ የሚያወርዱበት፣ ችግሩን የሚፈቱበት፣ በዳይንና ተበዳይን የሚዳኙበት፤ ጥፋተኛን የሚመክሩበት፣ የሚያስተምሩበት፣ ካሳ የሚያስከፍሉበት ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓት አላቸው፡፡

በአካባቢው ለግጭት ምክንያትና መንስኤ ከሚባሉ አበይት ጉዳዮች መካከል የከብት እና የፍየል ስርቆት (ዝርፍያ)፣ የድንበር ይገባኛል፣ የግጦሽ እና የመስኖ መሬት፣ በሚስት እና መሰል ተግባራት በሚፈጠሩ አጋጣሚዎች እና ክስተቶች ባለመተማመንና ባለመግባባት ግጭቶች ይፈጠራሉ፡፡ በተፈጠረው ግጭት መካከል የደም መፋሰስ እና የሰው ሕይወት ከጠፋ፤ ገዳይና የገዳይ ቤተሰቦች ወደ ጉሳ መሪና አስተዳዳሪያቸው በመሄድ የተፈጠረውን ክስተት በፍጥነት ያስረዳሉ፡፡ የሟች ቤተሰቦች የደረሰባቸውን መከራና በደል በብቀላ ለመመለስ ወደ ተግባር ከመግባታቸው በፊት የጎሳው መሪና አስተዳዳሪዎች ለእርቅና ሽምግልና እንዲቀርቡ ትእዛዝ ያስተላልፋሉ፡፡

በተያዘው የእርቅ ቀነ ቀጠሮ እለት የጎሳ መሪና አስተዳዳሪዎች፣ የአካባቢ ሽማግሌዎች፣ የገዳይና የሟች ቤተሰቦች፣ ቤተ-ዘመዶች እና የጎሳው አባላት በተገኙበት ፍርድ ይሰጣሉ፤

ወደ ገጽ 9 ዞሯል ...

# ህልም ለምን እናያለን?

## በታምሩ ደለለኝ



ለብዙ ሺህ ዘመናት ሰዎች ስለ ህልም ምንነት ስላለው ትርጉም እና ጥቅም ሲደነቁና ሲጠይቁ ኖረዋል። የዚህ አጭር ጽሁፍም ትኩረት ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ከተደረጉ ጥረቶች ውስጥ ጎልተው የወጡትን 3 ንድፈ ሀሳቦችን ማብራራት ነው። ከ3 ውስጥ ሁለቱ ሳይንሳዊ እይታ የያዙ ሲሆኑ የተቀረው ደግሞ መንፈሳዊ መሰረት ያለው ነው። ከዚህ በተጨማሪም በህልም ላይ ሳይንስ እርግጠኛ የሆነባቸውን አንዳንድ እውነታዎች አክያለሁ። እነሆ የህልም ንደፈ ሃሳብ በቅድሚያ፡-

### 1. ''ሱፐር ናቹራል'' ንድፈ ሀሳብ

የዚህ ንድፈ ሃሳብ እይታ ህልም ማለት ፈጣሪ (አማልክት) ለሰዎች ስለራሳቸው ወይም ወገኖቻቸው አሊያም ስላሉበት ወይም ስለሚመጣው ዘመን እጣፈንታ ለማሳወቅ መልክት የሚያስተላልፉበት መንገድ ነው ብሎ የሚረዳ ነው። በዚህም መሰረት መረጃው ሰዎች ራሳቸውን ሊከሰት ከሚችል አደጋ እንዲጠብቁ እና በአጠቃላይ ህይወታቸውን በተሥተካከለ መንገድ እነዲመሩ ይጠቅማል ብሎ ያምናል። ለዚህም እይታ ማጠናከሪያ የሚሆኑ ብዙ ምሳሌዎችን እንደ መጸሐፍ ቅዱስ ባሉ ቅዱሳን መጸሐፍት ውስጥ በስፋት ተጠቅሰው እናገኛለን። ለምሳሌ በመጸሐፍ ቅዱስ ውስጥ በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 41 ላይ የግብጹ ፈርኦን የተመለከተውን ህልምና ዮሴፍ የተባለ እብራዊ ብላቴና የሰጠውን ፍቺ እናገኛለን። ህልሙም በአንድ ሌሊት ፈርኦኑ መጀመሪያ ሰባት መልካቸው ያማረና የሰቡ ከብቶችን አየ። በመቀጠልም እነዚህን ሰባት ከብቶች ሌሎች ሰባት መልካቸው የከፉና የከሱ ሌሎች ከብቶች ሲውጧቸው አየ። ይህን አይቶ ከነቃ በኋላ እነደገና ተመሣሣይ ይዘት ያለው ህልም አየ። እሱም ሰባት የዳበሩ እሸቶች ከአንድ አገዳ ሲወጡና ቀጥሎም በምስራቅ ንፋስ የተመቱ፣የደረቁና የሰለሉ ሰባት እሸቶች ሲውጧቸው አየ። ዮሴፍም እነዚህ ህልሞች አንዳይነት ይዘት እንዳላቸውና ያም በመጀመሪያ ሰባት የጥጋብ አመታት እየመጡ እነደሆነ ከነሱም ለጥቀው ሰባት የድርቅ አመታት እንደሚከተሉ ፈጣሪ እያስጠነቀቀ መሆኑን ገለጸለት። ከዚህም ህልም ፍቺ የተገኘው መረጃ የግብጹን ፈርኦን የፖሊሲ እርምጃ እንዲወስድ ረድቶታል።እርምጃውም በጥጋብ አመታት ከሚገኘው ምርት ከአምስቱ አንዱን እጅ ህዝቡ ለፈርኦን እንዲያገቡና ከዚያም ውጪ የሚገኘው ትርፍ ምርት በጎተራ እንዲከማች አድርጓል። ሌላም ተጨማሪ ምሳሌ በትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ አራት ላይ ታላቁ የፋርስና ሚዶና ንጉስ ናቡከደነፆር እንደከብት ሰባት አመት ሳር እንደሚግጥ የሚያሳይ ይዘት ያለው ህልም እንዳለመና የፈጣሪን ኃያልነት ስላልተቀበለ ይህ መርገምት በሱ ላይ እንደሚደርስ ነብዩ ዳንኤል እንደፈታለት ተጠቅሶ እናገኛለን።

ምንም እንኳን በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ ባይገለጽም በአገራችንም ምን አይነት ንጉስ እንደሚነሳ ጥፋት ሆነ ልማት ምን እንደሚያመጣ የታዩ ህልሞች በአንዳንድ የታሪክ መጽሐፍት ውስጥ ተጠቅሶ እናገኛለን። ለምሳሌ ፖውሎስ ኞኞ በፃፈው አጤ ምንሊክ በሚለው መጸሐፍ ውስጥ አጤው ከገረድ እንደሚወለዱ፤ ገረዲቱ እናታቸው ከጭኗ ወስጥ በህልሟ ፀኃይ ሲወጣ መመልከቷንና ለማእድ ቤት ጓደኞቿ እንዳወራቻቸው ኋላም የንጉስ ሣህለ ስላሰ ሚስት (የምንሊክ አያት) ፍቺው ገብቷቸው ልጃቸው ማታ ይዟት እንዲያድርና ዘውድ ወራሹ እንዲፀነስ አድርገዋል። ሌላም ከዚሁ ታሪክ ጋር የሚመሳሰል የህልም ታሪክ ምሳሌ በዘውዴ ረታ ተፈሪ መኮንን፡-ረዥሙ የስልጣን ጉዞ በሚለው መጽሐፍ ውስጥ ተጠቅሶ እናገኛለን።

በዚህ መጽሐፍ ምንም እንኳን እንደተጠቀሰው አጤ ምንሊክ ስልጣናቸውን ለልጅ እያሱ አድገው እንዲወርሱና እንዲገዛ የተናዘዙ ቢሆንም

ወደ ገጽ 13 ዞሯል ...

# የሙርሲ ብሔረሰብ ባህልዊ ...

ከገጽ 8 የዞረ...

ባህላዊ የእርቅ ሥርዓት (Cultural Conciliation Rituals) ይፈፅማሉ። ከባህላዊ የእርቅ ሥርዓተ-ተግባር መካከል የተጣሉ ወገኖች በብቀላና በነፍስ ግድያ እንዳይፈላለጉ አንድ ጭብጥ (ጉርሻ) ጥሬ ማሽላ ወደ አፋቸው በማስገባት ያኝኩታል። የታኘከውን "እኝኩን" ጥሬ ማሽላ ካፋቸው አውጥተው በዳይና ተበዳይ በእጃቸው ይለዋወጣሉ (አካባቢው ቆላማ ስለሆነ የአገዳ እህል ያዘምራሉ)። የሥርዓተ ድርጊቱ አበይት ፋይዳ በአስተዳዳሪዎች የተሰጠውን ፍርድና ዳኝነት ባልቀበል፣ እርቅ ባፈርስ፣ ብከዳና እምነት ባጎድል እንደዚህ "እኝክ" ማሽላ "ቱም" (ፈጣሪ/አምላክ ማለት ነው) ያድቀኝ፣ ይሰባብረኝ፣ ለፍሬና ለቁም ነገር አያድርሰኝ… እንደማለት ነው።

በተከሰተው ግጭት የሰው ሕይወት ከጠፋ እና ከፍተኛ ጉዳት ከደረሰ፤ ከገዳይ ወገን ለሟች ወገን ልጃገረድ ትሰጣለች። ለተበዳይ ወገን የምትሰጠው ልጃገረድ "የጠፋውን ሰው ወልዳ ትተካላችሁ" በማለት ለሟቹ እናት በአደራ ትሰጣለች። የሟቹ እናትም አንገቷ ላይ ሞራ በማሰር የተሰጣትን አደራ ትቀበላለች። በአደራ የተቀበለቻትን ልጃገረድ ለሟች የቅርብ ዘመድ ትድራታለች። የተዳረችው ልጃገረድ ሁለቱን ወገኖች ወልዳና ከብዳ በደም፣ በዝምድ እና በጋብቻ ታስተሳስራለች። የሟች ቤተሰቦችና ጎሳዎች (ወገኖች) እርቁን በጋብቻ ለመፈፀም ካልፈለጉ ካሳው ከሰላሳ እስከ አርባ የሚገመቱ ቀንድ ከብቶችን በመስጠት እርቁ ይፈፀማል።

### 1.2 ባህላዊ የ"ዶንጋ" ፍልሚያ ጨዋታ

የሙርሲ ብሔረሰብ ከሚታወቁበት ባህልዊ የፍልሚያ ሥርዓተ ከበራዎች (Cultural Dueling Rituals) መካከል አንዱ የ"ዶንጋ" የሽመል ፍልሚያና ግጥሚያ (Donga Stick contestant) ጨዋታ ነው። የዶንጋ ባህላዊ የሽመል ፍልሚያና ግጥሚያ ጨዋታ በየዓመቱ የሚካሄድ ሥርዓት ነው (አዝመራ ከተሰበሰበ በኋላ ዓመቱ የምርትና የጥጋብ ዘመን ከሆነ ከ6 እስከ 8 ቀን ግጥሚያ ይካሄዳል፤ በአንፃሩ በቂ ምርት ያልተገኘበት ዓመት ከሆነ ለ4 ቀን ያህል ይቆያል፤ የቆይታ ግዜውም በአማካይ በሰኔ ወር ውስጥ (በተለይ ከ19 እስከ 26) ባሉት ቀናት የግጥሚያ ጨዋታው ይካሄዳል)። በፍልሚያ ሥርዓቱ የሚሳተፉ ያላገቡ እና እድሜያቸው ከ16 እስከ 32 የሚደርሱ የሙርሲ ወጣት ወንዶች ናቸው። ጨዋታው ከሚካሄድበት እለት ቀደም ብለው እራሳቸውን ለውድድር (ለፍልሚያ) ያዘጋጃሉ። ወጣቶቹ ከእድሜ እኩያ አቻዎቻቸው ጋር በንፅፅር ገጥመው ይፋለማሉ።

ለውድድሩ የተዘጋጁ ወጣቶች በዋናነት የከብት ደም እና ወተት እየጠጡ፣ (የሙርሲ ብሔረሰብ በተለይ ወጣት





ፎቶ ግ.ቁ2፡- ባህልዊ የ"ዶንጋ" ፍልሚያ ጨዋታ

ወደ ገጽ 12 ዞሯል ...

# ሶስት ጊዜ

በሂሩት አድማሱ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነጽሁፍ ት/ክፍል - የስነጽሁፍ መምህርት

nanihira@gmail.com

አበባ በእጅጉ ህመሟ ጠንቶባታል፡፡ በሽታዋ፣ ህመሟ ምግብ አይደለም፤ ውሃም አይደለም፤ ሰው ነው፡፡ ያውም የገዛ ልጇ፡፡ ከልጅነት እስከ ዕውቀት ያሳለፈችው ህይወት እንደተቀረጸ ምስል ወለል ብሎ ታያት፣ ውስጧን ያከበደውን ይህን የብቸኝነት ህመም ለማቃለል መፃፍ አለባት፡፡አዎ! መፃፍ አለባት ግን ምን ብላ ትጀምር፣ የሚያቅተው መጀመር ነው…

አንድ…….

ከአንዲት ምስኪን እናቷ ጋር በደሳሳ ጎጆ ያለ አባት የምትኖረው አበባ ባይደላትም፣ ባይመቻትም፣እንደልጅነቷ ፈንድቃና ስቃ ባትጠግብም እናቷን እየረዳች ትምህርቷን ተያይዛዋለች፡፡ እናቷ የልጇን ማደግ ተመልክታ አንድም ለመደጋገፍ ሁለትም የሚሰማትን ብቸኝነት ለማቃለል ስትል ከተዋወቀችው ሰው ጋር አብራ ለመኖር ወሰነች፡፡ ለልጇ ለመንገር ግን ቀላል አልሆነላትም፡፡

“አቢ አባትሽ ከሞተ እንሆ አስራ አምስት ዓመታት አለፉ፡፡ እንደምታይው ኑሮ እየተሻለ ሳይሆን እየባሰበት መጥቷል፡፡ እኔና እንቺ ብቻችንን ከምንሆን…” ሳትጨርስ አቋረጠችው፡፡

“እ እማ ምን አሰብሽ? እስኪ ንገሪኝ..”

“ላገባ ነው፡፡”

በማግስቱ የተባለው ሰው ጓዙን ጠቅሎ ከቤታቸው ገባ፡፡ በአበባ ህይወት ውስጥም መከራ አብሮ ገባ፡፡ የእንጀራ አባቷ አይነ ውሃ ከመጀመሪያው ቀን ያላማራት አበባ ሽሽትን ምርጫዋ አደረገች፡፡ በፍቅር የታነፀው ቤት በመጤው ተበጠበጠ፡፡ እናትም ልጇን አቅርባ ችግሯን ከመጠየቅ ይልቅ ማራቅን መረጠች፡፡ ምክንያቷ አዲሱ ባሏ ነበር፡፡ እሱን እንዳይከፋው ልጇን ፊት መንሳት ነበረባት፡፡ ለልጅ ፊት መስጠት አያስፈልግም በሚል ብሒል ታጠረች፡፡ ላይዘልቅ ፍቅር ሆነና ነገሩ ከመንፈቅ ያላለፈው ፍቅራቸው በመጠጥ ሃይል ይናጥ ጀመር፡፡ እንደ እባብ ቆዳውን አለስልሶ የገባው ቀና እውነተኛው ባህሪው ተገለጠ፡፡

“እንዴ ምን መሆንህ ነው? ስርዓት አባቴ እኮ ነህ!”

“መቼ ወለድኩሽ”

“ልጅህ እኮ እሆናለሁ፡፡ባትወልደኝም እናቴን ካገባህ ያው አባቴ ነህ፡፡”

“ባክሽ ወሬ አታብዢ፣ ይልቅ የፈለግሽውን ነገር ሳድርግልሽ የፈለኩትን ነገር አድርጊልኝ!”

“ምንድነው?”

“ደጋግሜ ጠይቄሻለሁ እሺ በይኝ”

“ለእማዬ እነግራታለሁ፡፡”

“እኔ እቀድምሻለሁ፡፡”

“አታፍርም? ስራህም እንደመልክህ ያስጠላል፡፡ ሳጥናኤል ነህ፡፡ ጭራቅ፤ እንዳትጠጋኝ”

በጥፊ አጮላት፣ ጮኸች፣ ደገማት እሪ አለች፡፡ እናቷ ስትደርስ ባሏና ልጇ የከረረ ፀብ ውስጥ ናቸው፡፡ የእናቷን ደስታ ላለመንጠቅ፣ የእንጀራ አባቷ የሚፈበርከውን ውሸት ላለመስማት ሮጣ ወጣች፡፡ አልተመለሰችም፡፡ ሁኔታውን ለጓደኛዋ ለቤቲ ነገረቻት፡፡ በአበባ ሁኔታ ያዘነችው ቤቲ መላ ፈለገች፡፡ ዘና ያለ ኑሮ የሚኖሩት የቤቲ ቤተሰቦች አበባን ለመያዝ እንቢ አላሉም ነበር፡፡ ከቤቲ ጋር አብራ እየዋለችና እየተማረች ራሷን ለመቻል ተፍጨረጨረች፡፡ ጥርሷን ነክሳ ተምራ ራሷን አወጣች፡፡ ሁሉም ነገር በፈለገችው መንገድ ሄደላት፡፡ ራሴን መቻል አለብኝ ስትል የጀመረችው ህይወት በካሳሁን አብሮነት ዘለቀ፡፡ ደስታ ተወለደ፡፡

ሁለት …..

አበባ ከካሳሁን ጋር የጀመረችው ህይወት ቆይታ ያደረገው ለሁለት አመታት ብቻ ነበር፡፡ ልክ እንደእንጀራ አባቷ ሁሉ አንድ ሁለት እያለ እያመሸ መግባት የጀመረው ባሏ ኑሮዋን ቀደም ብላ አማራው የጠፋችበትን ህይወት እንዲመስል አደረገው፡፡ ይሄኛ ከቀደመው የሚለየው በየቀኑ ዱላን በማከሉ ነበር፡፡ እናም ተማረረች አንድ ልጇን ይዛ ከቤት እንደወጣች ቀረች፡፡ ከልጅቷ የጀመረችው መሰደድ ዛሬም እጇን ይዛ ቀጠለችው፡፡ ይሁን እንጂ አበባ ለራሷም ሆነ ለልጇም መሆን አላቃታትም፡፡

ውበትና ደም ግባቷ እንዳለ፣ የማይኮሰኩሰው ጠባይዋ ሳይቀየር በፍፁም ፍቅር የወለደችውን ደስታ አሳደገችው፡፡ ብዙ ወንዶች ቢያንዣብቡባትም ጠንካራ ስብዕናዋን፣ ከሩቅ የሚስብ ውበቷን እየተመለከቱ ቢመኟትም ለማንም እጅ አልሰጠችም፡፡ ለልጇ ደስታ እንጂ ለራሷ መኖር አቆመች፡፡ ደስታ ቤቷን አሙቆና አድምቆ ሁሉንም አስረሳት፡፡ ለሱ ያላት ፍቅር የተለየ ነበር፡፡ ህይወቷን ሳትሰስት አፈሰሰችለት፡፡ ምንም ሳይጎድልበት፣ ደፋ ቀና ብላ የእሷ ሆድ ሳይሞላ እሱን አጠገበችው፤ እሷ እየበረዳት እሱን አሞቀችው፤ መድረስ የምትፈልግበት የትምህርት ደረጃ ባትደርስም ለከፍተኛ ትምህርት አበቃችው፡፡

በአዕምሮና በአካል የበሰለው ልጇ ከባህሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በማዕረግ ተመርቆ በአንድ የውጪ ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ ባህረኛ ሆነ፡፡ በጊዜ ብዛትና በምቾት ማጣት የጠወለገው የአበባ ገላ እያደር የበሰለ ብርቱካን መምሰል ያዘ፡፡ ልጇ ደስታ ብድር መመለሱን ተያያዘው፡፡ ለእናቱ ቤት፣ መኪና ገዛ፡፡ አበባም ጥሎ ያልጣላትን አምላክ አመሰገነች፡፡ ማታዋ ስላማረና ስለሰመረ ተደሰተች፡፡ ቤት ውስጥ የተትረፈረፈ ነገር ስለሆነላት ከፍ ያለ ነገር አሰበች፡፡ በቃ ለልጇ መንገር አለባት፡፡ ከጉዞ የሚመለስበትን ቀን በናፍቆት መጠባበቅ ያዘች፡፡ ደስታም እመጣለሁ ባለው ቀን ከተፍ አለ፡፡ ብቻውን ግን አልነበረም፡፡

“አቢ፣ ሰርፕራይዝ ላድርግሽ ብዬ ነው እጮኛዬ ናት ተዋወቁ፡፡”

“በጣም ደስ ይለኛል፤ አበባ የደስታ እናት፡፡”

“አለም”

ሶስት……

ቀለል ያለ ድግስ ተደግሶ በወር ውስጥ ጎጆ ተቀለሰ፣ የአበባም ህልም እውን ሆነ የመጨረሻ ደስታዋ የሚፈፀምበት ህልሟ የሚሰምርበት ጊዜ ደረሰ፡፡ ወር ወርን እየወለደ፣ አበባ የምትጠብቃትን ሴት ልጅ ሳይሆን ወንድ ልጅ አቀፈች፤ የልጅ ልጅ፡፡ አልተከፋችም ባልወልዳትም የልጄ ሚስት ልጄ ናት ስትል አሰበች፡፡

ሆኖም ብቸኝነቷን በልጅ ልጆቿ ለመግፈፍ ያሰበችው አበባ ደስታዋን ሳታጣጥም፣ገና ከጅምሩ የልጇ ሚስት የእናትና ልጅ ግኝኙነትና መተሳሰብ ያስቀናት ስለበነር፣ በራስ ወዳድነት መንፈስ ተሸብባ ልጅና እናትን ማራራቅ ሆነ ብላ ተያያዘችው፡፡ የባሏን ፍቅር ከሷና ከልጇ በቀር ማንም እንዲጋራት አልለገችም፡፡ አበባ ግራ ብትጋባም የጇ መራቅ እያሳሰባት፣ የልጅ ልጇ እየናፈቃት ተስፋ ሳትቆርጥ ሁኔታውን ለማስተካከል አንድ ሁለት ሶስት ጊዜ የልጇ ቤት ሄደች፡፡ የልጇ ሚስት ግን ፊት ነሳቻት፡፡ በፍቅር የተቀበለቻትን የደስታን እናት አለም በጥላቻ አራቀቻት፡፡ ምን እንደነገረችው ባይታወቅም ልጇ ደስታም ብዙ ዋጋ ከከፈለችለት እናቱ ይልቅ ሚስቱን አብልጦ እናቱን ተዋት፣ ብቻዋን ተዋት…

አበባ ሲበዛ ብቸኝነት ተጠናውቷት የቀን ከሌሊት ህመሟ ሆኖ ያሰቃያት ይዟል፡፡ እናም በማለዳ የቀሰቀሳትን የብቸኝነት ቅዝቃዜ ብዕር ጨብጣ መታገሏን ቀጠለች፡፡ ስትፅፈው የነበረውንም ማስታወሻ እንዲህ በሚል ሀሳብ ቋጨችው አለም… ህይወት… ወንድ … አንድ… ሁለት…. ሶስት…. መቼ ይሆን የተሻሉ የሚሆኑት!?

# ቄንጠኛው (ልብወለድ) ክፍል 3

አረጋዊ ሰለሞን
(2ኛ ዓመት የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ተማሪ)

Aregawisolo@gmail.com/
aregawi.slomon@facebook.com

ኑኃሚ ባርና ሪስቶራንት እንደደረሱ በመግቢያው በቀኝ በኩል ወዳለች አንዲት ትንሽዬ ጎጆ ውስጥ ገብተው ተቀምጠዋል እነቄንጠኛው፡፡ ጭፈራ ቤቷ በጨፋሪዎች፣ በጠጭዎች፣ በአጫሾች፣ በአስተናጋጆችና በሴተኛ አዳሪዎች ተጥለቅልቃለች፡፡ አራቱም ማዕዘኖቿ የወሲብ ስሜትን በሚቀሰቅሱ ፎቶዎች ተውባለች፡፡ ማዕዘኖቿ ላይ የተለጠፉት ምስሎች ይበልጥ ጎልተው እንደሚታዩ ደግሞ በእያንዳንዳቸው ምስሎች ጀርባ ትንንሽ ባለቀለም መብራቶች (ዜሮ አምፖሎች) በርተዋል፡፡ ጥቂት የማይባሉ ዲም ላይቶችም በሚሰጡት ብርሃን ኑኃሚ ይበልጥ እንዲያምርባት የማይናቅ ሚና ተጫውተዋል፡፡

‹‹ምን ልታዘዝ›› አለች በጣም አጭር ጥቁር ጉርድ በነጭ ቲ-ሸርት የለበሰችው አስተናጋጅ፡፡ ደረቷ መሃል ላይ የ‘v’ ቅርጽ ያለው ቲ-ሸርት እንደ አፈሙዝ ያነጣጠሩት ጡቶቿን ዓይን እንዲያርፍበት አድርጎታል፡፡ በዚያ ላይ የተቀባቸው ሽቶ ወደ አፍንጫ ሲደርስ ከእሷ ጋር ለማደር ያስመኛል፡፡ ውብ ነች፡፡ እድሜዋም ለጋ ነው፡፡

‹‹እ… ሶስት ደብል ብሔራዊና ሶስት ቢራ አምጭልን፡፡ ቢራው ካስትል ቢሆን ደስ ይለናል፡፡›› አለ ኤርሚያስ አንዴ ከንፈሮቿን አንዴ ደግሞ ጡቶቿን እየተመለከተ፡፡
‹‹ይቅርታ ካስትል ለጊዜው ጨርሰናል፡፡››
‹‹ዳሽንስ?››
‹‹ዳሽን አለ፡፡››
‹‹በቃ እሱን አምጭልን፡፡›› አሁንም ኤርሚያስ ነበር የተናገረው፡፡ አስተናጋጇ ትእዛዙን ተቀብላ ዳሌዋን እያወዛወዘች ስትሄድ ሶስቱም በስሜት ዓይን ተመልክተው ተመኟት፡፡

************** *********** **************

ጥቂት የናይጀሪያ ሙዚቃዎች ከተሰሙ በኋላ አማርኛ ጀመሩ፡፡ ‹‹ከመኮንን ድልድይ ከእንጨት ፎቁ በላይ … ሲመሽ እንገናኝ… መጣሁ አንቺን ብዬ ሳይከብደኝ እርምጃው በሳባ ደረጃው… ትም ትርርም ትርርም ትርርም …›› የቴዲ ዘፈን ቀጠለ፡፡ ብዙም ሳይቆይ ያዘዙትን ቢራና ጅን መጣላቸው፡፡ ጅኑን አነሱና ‹‹ላስደሳች ሕይወት ለተሻለ ውጤት ፅዋችንን እናንሳ! ችርስ፡፡›› ብለው ሶስቱም በአንድ ትንፋሽ ጨለጡት፡፡ ቴዲም የደስታቸው ተካፋይ ይመስል አሁንም መዝፈኑን ቀጠለ…

‹‹ባሳሪም ኮት ላይ ያንን ቀጭን ኩታ ጣል አድርጌ … በመኮንን ድልድይ ልምጣ በደረጃው በፒያሳ አርጌ … በፍቅር ማነቂያው ዶሮ እንዳይል በከንቱ እሪ አንቺን ወዶ … ክራሩን ስትሰሚ ብቅ በይ

ወደ ገጽ 14 ዞሯል

# ህልም ለምን እናያለን?

ከገጽ 13 የዞረ...

### ሀ. ሁሉም ሰው ህልምን ያያልን?

ህፃንም ሆነ አዋቂ ሴትም ሆነች ወንድ፣ እይነስውርም ሆነ አይና ብቻ ማንኛውም ሰው ህልምን ያያል። ጥናቶች እንዳውም እያንዳንዱ ሰው በአንድ ሌሊት ብዙ አይነት ህልሞችን እንደሚያና እያንዳንዱም ህልም በአማካኝ ከ5-20 ደቀቃ እንደሚረዝም አረጋገግጠዋል። በዚህም በመነሳት በአለም ላይ ካለው ያንድ ሰው አማካይ እድሜ ውስጥ 6ቱ አመት የሚሆነው ህልም በማየት እንደሚጠፋ ይገመታል።

### ለ. ያየነውን ህልም እንረሳለን?

ምንም እንኳን ለብዙ ህይወት ዘመናት ብዙ ህልሞችን ብናይም 95% የሚሆነውን ወዲያውኑ እንረሳዋለን። ለዚህም ዋነኛ ምክንያቱ እንደ ታዋቂው የህልም አጥኚ አለን ሆብሰን ከሆነ “ፍሮንታል ሉብ” የተባለው አዲስ መረጃን የመመዝገብና የማከማቸት ስር ላይ የሚጠመደው የአንጎል ክፍል በእንቅልፍ ሰአት ንቁ ስላልሆነ መረጃውን ስንነቃ ከአይምሮአችን እናጣዋለን።

### ሐ. ህልሞቻችን ባለቀለም ናቸውን?

80% የሚሆኑት ህልሞች ባለቀለም ሲሆኑ የተወሰኑ ሰዎች ግን ከነጭና ጥቁር ህልም ውጭ አይተው እንደማያውቁ ይገልጻሉ።

### መ. ፆታዊ ልዩነቶች አሉን?

ጥናቶች እንደሚሳዩት ከሆነ ወንዶች ሴቶችን ከማለም ሁለት እጥፍ በላይ ስለ ወንዶች ያልማሉ። ነገር ግን ሴቶች ሁለቱን ፆታዎች በእኩል መጠን በህልማቸው ያያሉ።

### ሠ. እንስሳት ህልም ያያሉን?

ምንም እንኳን እርግጠኛ መሆን ባይቻልም እንስሳት ህልም ሊያዩ የሚችሉ ፍንጮች አሉ። እንዳንዴ ውሾች ተኝተው ሲፈራገጡ፣ ሲንቀሳቀሱ ማየታች ይህን የሚደግፍ ይመስላል።

### ረ. በህልም ደስታ ወይስ ጭንቀት ይበዛል?

ከ50,000 ህልሞ በላይ በመሰብሰብ ትንተና ያካሄደው ዊሊያም ዶሞሆፍ በህልም ወቅት ከደስታ ይልቅ የጭንቀት ይዘት እንደሚበዛ ማወቅ ችሏል።

### ሰ. ሁሉም ሰው አንድ አይነት ህልምን ያያልን?

ምንም እንኳን ህልሞቻችን እንደ ኑሮአችንና፣ እድሜያችን ሁኔታ ቢለያዩም የተወሰኑ ይዘቶች ግን በተመሳሳይ መልኩ በህልም ይከሰታሉ። ለምሳሌ ሲሳደዱ፣ሲጠቁና ሲበሩ ማየት የተለመዱ ናቸው።

# “የተማረ ሰዉ ይግደለኝ” እንደ እኔ መረዳት

## ክፍል ሁለት

በፀጋ ጥበቡ

ባለፈዉ እትም ላይ ቀደም ያሉትን የሃይማኖታዉያንና የዘመናዉያንን /የሳይንሳዉያንን/ ምሁራን ጠባይ ለማየት ሞክረን ነበር:: የዘመናችንን ደግሞ እነሆ፣ ማሳሰቢያ ያለፉት ሁሉም ያሁኖቹም ሁሉም እንደተገለጸዉ ናቸዉ ለማለት ሳይሆን በአብዛኛዉ ለመግለጽ ያህል እንደሆነ ይታሰብ:: አሁን አሁን እንደ እኔ እምነት በሁለቱም ሰልፎች /በመንፈሳዊዉም በዘመናዊዉም/ የተሰለፍነዉ በአብዛኛዉ /ሁሉንም አላልሁም/ ከላይኞቹ በተቃራኒዉ የምንኖር ይመስለኛል:: የሁለቱም /የመንፈሳዊዉም የዘመናዊዉም/ ሰልፍ ገጸ ባሕርያት መማርም ሆነ ማንበብ እጅግ የሠለቸን ሳንጀምረዉ የጨረስን ያለዕድሜአችን ከእዉቀትና ከንባብ ከመልካም ሥራና ዓርዓያነት ወዘተ ራሳችንን በጡረታ ያገለልን ይመስለኛል:: በግልብ እዉቀት በእጅጉ የምንማቅቅም ይመስለኛል:: አንዳንዶቻችን ከባድ የአቋም መዋለል ዓይን ያወጣ የማይሰነብት ተለዋዋጭ ወገንተኝነት የተጠናወተንም ይመስለኛል :: ዓይኖቻችን እጅግ የደቀቁ በድንግዝግዝ ዉስጥ ያሉ ጆሮዎቻችን በፍጹም መስማት ከሚፈልጉት ዉጭ መስማት የማይፈልጉ ላሰማማቸዉ ሚዛናዊነት የጎደላቸዉ እጅግ ትንሽ ጭንቅላት ግዙፍ ሆድ ተሸክምን የምንጓዝ ይመስለኛል::

ሁለቱን ሰልፎች በተናጥል ለማየት ያህል

አንዳንዶች /አሁንም ሁሉንም አላልሁም/ የሃይማኖት “መምህራን” በሁለት በኩል የተጎዱ ናቸዉ:: የሃይማኖቱን መሠረት በጥልቀት የተገነዘቡም አይደሉም በመልካም ሥነምግባራቸዉም የተመሰገኑ አይደሉም:: በሃይማኖታቸዉ ለራሳቸዉ ተምታቶባቸዉ ሰዉን የሚያምታቱ ሲሆን በሥነ-ምግባርም በኩል በሁለት ቢላዋ የሚበሉ ናቸዉ:: በሁለት ገመድ የተወጠሩ ማለትም የቤተ መንግስቱንም የቤተ እምነቱንም ፈቃድ /የማይጣጣሙ ወይም እጅግ የሚቃረኑ ፈቃዳትን ለማለት ነዉ/ ለመፈጸም ባንድ ጊዜ ሁለት ዛፍ ላይ የመዉጣት ያህል የሚዳክሩ ናቸዉ:: እንደበቶቻቸዉ መራራና ጣፋጭ ባንዴ የሚፈስባቸዉ ጉድጓዶች፣ ባንዴም በለስና ኩርንችት የሚያፈሩ፣ ካልተጠበቁበት ቦታ የሚገኙ ናቸዉ:: የዕምነት ተቋማቱም ሆኑ ሕዝቦች አትወክሉንም ቢሏቸዉም እንኳ የቆሙለት ሥጋዊ ጥቅማቸዉ እንዳይቋረጥ የማይወጡት ዳገት የማይወርዱት ቁልቁለት የለም:: ግፋ ሲልም አንዳንድ ጥቅማም ባለስልጣናትንና የዋህ ምዕመናንን እንደመሸሸጊያ ተጠቅመዉ ላለመልቀቅ ይታገላሉ:: ብዙዎቹ የማይሞላ ኪስ ያላቸዉ ፈሪሃ እግዚአብሔር ይቅርና ይሉኝታ እንኳ የሌላቸዉ ናቸዉ:: እንደ ቅዱሱ መጽሐፍ “ዉኃ የሌለባቸዉ ምንጮች በነፋስ የተገፉ ደመናዎች ናቸዉ::” ስለዚህም እነዚህን ”መምህራንን” ሰዉ “የተማረ ሰዉ ይግደለኝ” ሲል ምንም ምሥጢራዊ ፍች አያስፈልገዉም በቁሙ በሃይማኖት መምህርነት ስም ተጫወቱብኝ አታለሉኝ በነፍስም በሥጋም ገደሉኝ ማለቱ ነዉ እላለሁ::

አንዳንዶቻችን /እዚህም ላይ ሁሉንም አላልሁም/ ዘመናዊዉን ተማርን አወቅን የምንልም ከላይ ከተገለጸዉ ከመንፈሳዉያን መምህራን ብንብስ እንጅ የምንሻል አይደለንም እላለሁ:: ለትዉልዱ ሊተላለፍ የሚችል ጽንሰ ሀሳብም ሆነ ተግባር /THEORY AND PRACTICE/ የለንም:: ስልቹ ነን:: በዲግሪ ላይ ዲግሪ ባናት ባናቱ እንደ እምቧይ ካብ የምንከብ፣ እሱንም ምንም ሳንማርና ጊዜ ሳንጠብቅ ባንዴ ዝም ብለዉ ቢያድሉን የምንወድ፣ አንድ ምክረ ሀሳብ /PROPOSAL/ ለማዘጋጀት የማንሞክር የሰዎችን ሥራዎች ቀድቶ በማተም /COPY AND PASTE/ የምንኖር፣ ከራሳችን አስተዋጽኦ የሌለን፣ እንዲኖረንም የማናስብ ጦርነቱ ሳይጀመር የተማረከ ሠራዊትን የምንምስል ነን:: ያለችዋን እንጥፍጣፊ ዕዉቀት እንኳ በትክክል ለማስተላለፍ የታከተን፣ ስልችት ምርር ያለን፣ አለማወቃችንን በመሳደብ በመናደድ ለመሸፈን የምንሞክር እዉነቱን ለመናገር ወይም ለመተቸት የማንደፍር ሞራሉ የሌለን፣ ያለመድረካችን የቆምን ነን ብል ያንስ እንደሆን እንጅ ማጋነን አይሆንም:: ብዙዎቻችን በዓላማ ለመጓዛችን እርግጠኛ አይደለሁም:: ለምንሠራበት ተቋምም ሆነ ለሀገሪቱ ወይም ለኅብረተሰቡ ምን ማበርከት እንዳለብን የምናስብ አይመስለኝም :: አንድን መርህ ለመተቸት ወይም ለመተንተንና ለሀገር ለወገን ወይም ለተቋም ያለዉን ጠቀሜታ ለመመዘንና አስተያየት ለመስጠት መሠረታችን እዉቀት መሆን ሲገባዉ ይህን ሙሉ በሙሉ እንረሳና ለአስተያየታችን ስለሚሰጠዉ ግብረ መልስ /በተለይ የገዢዎችን ግንባርና የባዕለ ጸጎችን ኪስ/ እያሰብን በፍርሃት እንጨነቃለን አለዚያም ጭራሽ ያንን ለማድረግ አቅሙም ሀሳቡም የለንም:: እናም የተማረዉን ሰዉ ቦታ ይዘን ኅብረተሰቡን እንገድላለን ሀገሪቱንም እንጥላለን በፍርሃት ተዉጠን በጥቅማ ጥቅም ታዉረን ከእዉነትና ከእዉቀት ርቀን ወይም ተጣልተን ኑሮን እየገፋን እንደሆነ ይሰማኛል:: ስለዚህም እነዚህንም ”ምሁራን” ኅብረተሰቡ “የተማረ ሰዉ ይግደለኝ” ሲል ምንም ምሥጢራዊ ፍች ሳያስፈልገዉ እንደላይኛዉ ሁሉ በቁሙ በምሁርነት፣ በሊቅነት፣ ወይም በመምህርነት ስም ነገዱብን፣ ተጫወቱብን፣ አታለሉን፣ በነፍስም በሥጋም አጠፉን፣ ሰድበዉ ለሰዳቢ ሰጡን፣ ማለቱ እንደሆነ እረዳለሁ:: አዎ እዉነቱን ነዉ ሕዝባችን ብዙዎች ሀኪሞቹ፣ የሕግ ባለሙያዎቹ፣ የሂሳብ ባለሙያዎቹ፣ የታሪክ ጸሐፊዎች፣ መምህራኑ፣ መሀንዲሶቹ፣ ደራሲዎቹ እና ሌሎቹም የሙያ ባለቤቶች በሙያዉ ብቁ ዕዉቀት ባለመያዝ ወይም በታላቅ ፍርሃት ዉስጥ ተደብቀን እየገደልነዉ ነዉ:: ከችግሩ በተቃራኒ እየቆምን እየገደልነዉ ነዉ:: ከእዉነተኝነትም ከፍትሃዊነትም ሩቅ ነን:: መዐዳችንን ብቻ የምናገለግል “የተማርን” ገዳዮች ነን::

ለማጠቃለል ያህል ፍርሃት ለአሁኑ ዉድቀታችን ትልቁን ድርሻ እንደሚይዝ እገምታለሁ:: ከምር ብዙዎቻችን መንፈሳዉያንም ዘመናዉያንም በታላቅ ፍርሃት ዉስጥ ነን:: እንፈራለን የሚለዉ አይገልጸዉም:: መፍራት ራስንም ኅብረተሰብንም ይገድላል:: ፍርሃት ደግሞ ከእዉቀት ማነስ፣ ጥቅማም ከመሆን / አእምሮን ክዶ ለሆድ ብቻ ከማደር/፣ ራስን ብቻ ማዕከል አድርጎ ከመጓዝ፣ ሀገርን ወገንን ከመዘንጋት፣ ዓላማን ከማጣት የሚመጣ መጥፎ በሽታ ነዉ:: የምናራምደዉ አቋም እዉነት መሆኑ / ከደመቀበት የማያጨበጭብ/፣ ከአምላክ የማያጣላ፣ ሀገርን ወገንን የሚጠቅም፣ መጥፎ ሥራንና ድንቁርናን የማይሸከም መሆኑ ብቻ ይበቃዋል:: እንደ እኔ ከሆነ ሌላ መለኪያ አያስፈልገዉም:: ስለዚህም ባጭር አገላለጽ “የካህን ወይም የሼህ፣ የምሁር፣ የጥበብ ሰዉ /የደራሲ የገጣሚ ወዘተ/ ፈሪና የአህያ እዉር ለማንም ለምንም አይጠቅምም” እንደሚባለዉ ፍርሃት ዉበት አልባ ያደርጋል መልከ ጥፉ ያደርጋልና ብናስብበት እላለሁ:: እናም ፈጥነን ፍርሃት ዉስጥ የከተቱንን ድክመቶች አጥፍተን እኛን ከገባንበት የፍርሃት ጉድጓድ ለማዉጣት እንጣር ትውልዱንም አንገት አናስደፋዉ “ሕይወት አጭር” ናትና!

# የዩኒቨርሲቲው ተማሪ ማስታወሻ

ከገጽ 6 የዞረ...

ቆዩና፣ሁለት ሰዓት ሲሆን የቴሌቪዥን ዜና ለመከታተል ወደ ቴሌቪዥን መመልከቻው ማዕከል በአንድነት በመሄድ ዜና ስናዳምጥ ቆይተን በመመለስ በእኔ ላይ የደረሰውን መጥፎ አጋጣሚ ለማስረሳት የጋራ ጨዋታ ስናደርግ አመሽንና ቀስ በቀስ ሁላችንም ተኛን:: በዕለቱ ከደረሰብኝ የስርቆት ጥቃት ጋር ተደማምሮ አዕምሮዬ ሊረጋጋ ባለመቻሉ እንቅልፍ የሚባል ነገር በዐይኔ አልዞር አለ። እንቅልፍ እንዲወስደኝ ያላሰብሁት ያልሞከርሁት ነገር የለም እንቅልፍ እምቢ ሲል ከአንድ ጀምሮ መቁጠር የሚለውን ዘዴ በመጠቀም እስከ ብዙ ሺ አሃዞች ቆጠርሁ። እሱም አልሠራም። እንዲያውም መቁጠሩ ሰለቸኝ እንጅ እንቅልፍ ሊወስደኝ አልቻለም።

# የሙርሲ ብሔረሰብ ባህልዊ ...

ከገጽ 9 የዞረ...

ወንዶች በከብት አንገት ላይ የሚገኝ የደም ስርን በመብጣት ከእንጨት በተፈለፈለ ጎድጓዳ እቃ፣ ግማሽ በግማሽ በተሰነጠቀ ጎድጓዳ ቅል ወይም ሽክላ በመጠቀም የቀዱትን ደም በትኩሱ በርከክ ብለው ግጥም አድርገው ይጠጣሉ) የማሽላ ገንፎ እየተመገቡ፤ ለሳምንታትና ለወራት የአካል ብቃት እና የስነ-ልቡና ዝግጅት ያደርጋሉ፡፡ ዝግጅቱም የሽመል አያያዝ ሥርዓት፣ የመመከት፣ የመከላከል፣ የመሰንዘር፣ የማጥቃት እና የማፈግፈግ ስልትን (ወደኋላ የመሸሽ ዘዴን) ይማራሉ (ለፍልሚያ የሚይዙት ሽመል ከ2 እስከ 2.15 ሜትር ይረዝማል፤ ክብደቱም ከ700 እስከ 800 ግራም ይመዝናል)፣ ፡፡

በዚህ ሥርዓተ-ፍልሚያ ቅልጥፍናውን፣ ብቃቱን፣ ጥንካሬውን፣ ፅናቱን እና ጅግንነቱን (Endurance and Hero) ያስመሰከር ይወደሳል፤ በአንፃሩ በፍልሚያው ያልተሳተፈ ወጣት እንደ ደካማ እና ፈሪ ስለሚቆጠር የሙርሲ ወጣት ቆነጃጂት እና ልጃገረዶች ለትዳር አይመርጡትም ወይም የልጅቷ ቤተሰቦች ጋብቻውን አይቀበሉም፡፡ ስለሆነም የሙርሲ ወጣቶች ሚስት ለማግባት በዶንጋ ፍልሚያ ጨዋታ ላይ መሳተፍ ግዴታ ነው፡፡ በሙርሲ ብሔረሰብ ባህልዊ የጋብቻ ሥርዓት ሲደረግ ወንድ ልጅ ለጥሎሽ 38 የሚደርሱ ከብትና ፍየል ከአንድ ጠመንጃ ጋር ለሙሽሪት ቤተሰብ ይሰጣል፡፡

የሙርሲ ወጣት ወንዶች የሳምንታትና የወራት ዝግጅታቸውን አጠናቀው፤ ለፍልሚያ ያዘጋጁትን ሽመል (በሥርዓትና በጥንቃቄ የተመረጠ ቀጥ ያለ ብትር) በመያዝ ወደ ግጥሚያ ቦታው ያመራሉ፡፡ የፍልሚያ (Dueling) ሥርዓተ-ጨዋታው ከሰፈር ይጀምራል፡ ፡ ወጣቶች በሰፈር (በቀጣና)፣ በቀበሌ፣ በወረዳ እና በዞን ዙር ተደጋጋሚ ግጥሚያ አሸንፈው ለመጨረሻ ፍልሚያ እና የጀግኖች ጀግና ለመባል ኮይሴ (ንጉሱ) በሚጠራው ሰፈር ተፋላሚዎች ይገናኛሉ (ማለትም፤ እንደአፍሪካ፣ አውሮፓና የአለም ዋንጫ እግር ኳስ ጨዋታ ማጣሪያውን አልፈው ደረጃ በጀረጃ ተጋጣሚያቸውን አሸንፈው ለመጨረሻ የዋንጫ ፍልሚያ የሚቀርቡ አገሮች እንደማለት ነው)፡ ፡ የፍልሚያውን ሥርዓት እና ዳኝነት የሚመሩ በአካባቢው የተመረጡ፤ ከዚህ በፊት በጀግንነታቸው የታወቁ ጎበዞች ጨዋታውን ይዳኙታል፤ ይመሩታል፡፡ በአንድ ፍልሚያ ዙር ከአስር በታችም ሆነ በላይ ተጋጣሚ ጥንዶች ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ተፋላሚዎች እና ዳኞች እየተፈራረቁ የጨዋታው ሥርዓት ከጧት እስከ ማታ ይካሄዳል፡፡

በመጨረሻው የዶንጋ ፍልሚያ ጨዋታ እለት በዋናነት የብሔረሰቡ ባህልዊ አስተዳዳሪዎች፣ መንፈሳዊ አባቶች፣ የጎሳ አባላት፣ ትዳር ያልመሰረቱ ወጣት ሴቶች ታዳሚና ተመልካች ናቸው፡፡ በተለይ ወጣት ሴቶች ለፍልሚያ የመጡ ቡድኖችን (ጀግኖችን) በማበረታታት፣ ወኔያቸውን በመቀስቀስ፣ ጀግና መሆናቸውን በማወደስ በዜማና በግጥም ያበረታቷቸዋል፡፡ ለፍልሚያ የሚቀርቡ ወጣቶች ሙሉ የሰውነት አካላቸውን በወራጅ ውሃ (በወንዝ) ታጥበው በነጭ፣ በቀይ ወይም ጠመኔ መሰል አፈር ሰውነታቸውን ጌጠኛ እና መልከኛ በሆነ ምስልና ቅርፅ አስጊጠውና አኾርጎርጉረው ለፍልሚያ ይቀርባሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ያላገቡ የሙርሲ ወጣት ሴቶችን እይታ ለመግዛት እና ለመማረክ ይጠቀሙበታል፡፡ በተለይ ለመጨረሻ ፍልሚያ የቀረቡ ወጣቶች በከፍተኛ ጥረት፣ ፅናትና ጀግንነት (Endurance and Heroic) አሸንፈው፡ በብሔረሰቡ ባህልዊ አስተዳዳሪ እና መንፈሳዊ መሪ ከተሸለሙ እና ከተመረቁ በኋላ ባህላዊ የጭፈራ ሥርዓት ተዘጋጅቶ በደስታ ይጨፍራሉ፡፡ በእለቱም ባላገቡ ወጣት ቆነጃጂት ይመረጣሉ፡፡

ወጣት ያላገባች የሙርሲ ሴትም የተፋላሚውን ተክለሰውነት፣ የአጋጌጥ ስልት፣ የጀግንነት ፍልሚያና ግጥሚያ ብቃት፣ ንቃት፣ ጀብደኛነት በማጤን ለተማረከችለት ወጣት የአንገቷን ጨሌ አውልቃ ታጠልቅለታለች፡፡ ወጣቱም ተመራጭና ተወዳጅ በመሆኑ ክብርና ደስታ እየተሰማው፡ ጨሌ ባንገቱ ላጠለቀችለት ልጃገረድ ባህላዊ የጋብቻ ሥርዓቱን ፈፅሞ በጋብቻ ይጣመራሉ፡ ጎጆ መስርተው አብረው መኖር ይጀምራሉ፡፡ የዶንጋ ባህላዊ የፍልሚያ ጨዋታ ለተፋላሚው በህይወት ዘመኑ አንድ ጊዜ የሚፈፅም ተግባር ነው (የትዳር ማግኛ እና መመስረቻ መንገድ ነው)፡፡

በጨዋታው ግጥሚያ የጭንቅላት መፈንከት፣ የአጥንት መሰበርና መሰንጠቅ፣ የአካል መጉደል እና ለሰው ሕይወት መጥፋት ምክንያት የሚሆኑ አጋጣሚዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ ይህን ጉዳትና ችግር በመገንዘብ ይመስላል "ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ነው!" ተብሎ ሾላ በድፍኑ የተፈረጀው፡፡

ብሔረሰቡ ይህን ድርጊት እንዲፈፅም ያስገደዱት ታሪካዊ፣ ልማዳዊ እና መንፈሳዊ ምክንያቶች ምንድን ናቸው? ይህን ባህላዊ ፍልሚያ በአካባቢው አስተዳደር እና በመንግስት መመሪያ እንዲያቆሙ ቢገደዱ በብሔረሰቡ አባላት ላይ የሚያደረሰው ስነልቡናዊ ጫና፣ የእሴት መለወጥ እና የከየትነት ጥያቄ ማስነሳትና አለማስነሳቱ በመስኩ ምሁራን ተጠንቶ ምላሽ ቢሰጠው መልካም ነው፤ በሕግ እና በሥርዓት ከማስገደድ፡፡

የጥቅም እና ጉዳቱን መጠን ከባህሉ ተግባሪና ተሳታፉ ብሔረሰብ አለበለዚያም በመስኩ ተመራማሪዎች የሚሰጡ ምክንያቶችን እና የመፍትሔ ምጋቤ ምላሾችን በመያዝ ስለጥቅምና ጉዳቱ ከብሔረሰቡ ባህላዊ አስተዳዳሪ አባላት ጋር መግባባት እና መስማማትን ይጠይቃል፡፡ ስምምነቱም በአዋጅ፣ በመመሪያ እና በመሰል ተግባራት ተገድቦ እና በተፅዕኖ እንዲቀበሉት ከማድረግ የለውጡን ሂደት ተቀብለው፣ ጉዳትና ጠቀሜታውን ለይተው፣ በቂ ግንዛቤ አግኝተው በፍቃዳቸው እንዲወስኑ ማድረግ መፍትሔ ይመስለኛል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ነባሩ ባህል ምን ነበር? አሁን በምን አይነት ሁኔታ ላይ ይገኛል? የዘመኑ አስተሳሰብ እና የብሔረሰቡ አለማዊና መንፈሳዊ ግንዛቤ ምን ይፈልጋል? የሚሉ ጥያቄዎች ምላሻ ማግኘት አለባቸው፤ በደምሳሳው "ጎጂ ነው!" ከማለት፡፡ ስለሆነም አሁን ያለው ባህላዊ የዶንጋ ፍልሚያ ጨዋታ ሥርዓት እና ተግባራት በጥንቃቄ ተሰንደው፣ ተጠንተው እና ተመርምረው ጉዳት እና ፋይዳቸው ተለይቶ እሴትነታቸው ቢጠበቅ መልካም ነው፡፡

ከዚህ አንፃር ከባህሉ ተግባሪና ተሳታፊ ውጪ የሆነ ግለሰብ ወይም ቡድን ግላዊ የህይወት ተመክሮውን መሰረት አድርጉ የሌሎችን ልማድ፣ ልምድ፣ ሥርዓት፣ አምልኮና መሰል ተግባራትን ለይቶና ነቅሶ በማውጣት መፈረጅ እና በአዋጅ መደንገግ አንቱታን አያተርፍም (ማስተማር እንጂ!)፡፡ ስለዚህ በጨዋታው ሂደት እና ክስተት የተጎዱ ተፋላሚዎችን ስብራት ለመጠገን እና ህመማቸውን ለመፈወስ የአካባቢው ባህል ቱሪዝም እና የህክምና ባለሙያዎች በተቀናጀ እና በተደራጀ መልኩ የበኩላቸውን እገዛ እና እርዳታ ቢያደርጉ መልካም ይመስለኛል (የብሔረሰቡን ልማድና እሴት እንደ ቱሪስት ምንጭ ሃብትነት ከመጠቀም ባሻገር መጠበቅና መንከባከብም ያሻል)፡፡ ጨዋታውን የሚመሩ ባህላዊ ዳኞች በንቃትና በብቃት ተከታትለው የደከመና የተጎዳ ተፋላሚን የመለየትና ጨዋታውን የማስቆም ሃላፊነት አላቸው፡፡ እነዚህ ባለሙያዎች ከሚመለከታቸው ባህል ነክ ሙያተኞች እና አስተዳደር አካላት ጋር ተገናኝተው ጉዳት ሊያደረሱ የሚችሉ ምክንያቶችን በመለየት የጨዋታውን ሥርዓት ማሻሻል እና አብዛኞቹ ባህላዊ እሴቶች ተጠብቀው እንዲቀጥሉ ቢደረግ መልካም ይመስለኛል፡፡

(ምንጭ፡-የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች (ብሔረሰቦች) ምክር ቤት በ2004ዓ.ም የታተመ ፕሮፍይል፡፡ ከጅንካ ከተማ ሙዚየም፤ በ2004ዓ.ም ካሰባሰብኳቸው መጣጥፎች፡፡ Turton, D.(1970). "The Social Organization of the Mursi; A Pastoral Tribe of the Lower Omo Valley South West Ethiopia". University of London;

# Dealing with Sexual Problems

continued from page 15

erection, and he worries that he is becoming impotent. This concern may impair Kebede's performance the next time he is sexually intimate, making it even more difficult the time after that. This process may soon escalate into a dysfunction. Clinicians use the term *spectatoring* to refer to the experience in which the individual feels unduly self-conscious during sexual activity, as if evaluating and monitoring his performance during the sexual encounter.

In general, it is crucial to understand and accept any sexual difficulty you may experience because sexual problems are not be shameful secrets and should not create feelings of inadequacy or hopelessness. You are responsible for addressing your sexual problems, because they can successfully be dealt with. In this regard, having the understanding, motivation, and resources to deal with and resolve sexual problems will greatly enhance your sexual health and satisfaction. It is also important to keep in mind that sexual dysfunctions can be physically as well as psychologically based, and that often there is an interaction between physical and psychological factors. To understand sexual dysfunctions and effectively resolve them, therefore, it is helpful to gain a perspective on the factors that contribute to healthy sexual functioning.

In this way, you should be cognizant of all the factors influencing male, female and couple sexuality and you could successfully address the problem using all your resources. Unless you comprehensively address problems and devote time and energy to healthy sexuality, you are likely to regress to problematic sexual behavior.

At last, the various sexual dysfunctions or problems could be effectively treated using psychotherapeutic interventions (that include behavioral, cognitive-behavioral, couple or sex therapy techniques and psychosexual skills) as well as bio-medical interventions (such as medications or using drugs such as viagra).

The most important issue to bear in mind is, however, before using any medication (such as Viagra), you need to consult with your physician about all the medications you take and their possible sexual side effects (*I will discuss Viagra in my next article*).

# ህልም ለምን እናያለን?

ከገጽ 9 የዞረ...

በጐጃም፣በጐንደር በሸዋ የሚገኙት መነኮሳት እናትና አባታቸውን በልጅነት ያጡትና ያለወንድም እና እህት በብቸኝነት ያደጉት ተፈሪ መኮንን /የወደፊቱ ቀዳማዊ ሐይለ ስላሴ/ እንደሚነግሱ ህልም አይተው እንደነበርና በሰፊው በህዝቡ ዘንድ በዘመኑ ይወራ እንደነበር ዘውዴ ረታ በሰፊው አትተውታል፡፡ በተለይም በደብረሊባኖስ ገዳም ከአለም ርቀው ከሚገኙት አበቅቴዎች መካከል አባ ሥርገ-ወቃል የተባሉት መነኩሴ ራስተፈሪ የምነሊክን አገር ጠቅልለው ከአርባ አመት በላይ እንደሚገዙና መጨረሻቸው ግን ምን እንደሆነ ማየት እንዳልቻሉ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡

የዚህ ህልም በዘመኑ መነገር ከልጅነቱ ጀምሮ ተፈሪ መኮንንን በቅጥነቱና በእጥረቱ ለሚጠላውና ለሚንቀው አልጋወራሽ ልጅ እያሱ ትልቅ የቅናት ምንጭ ሆኖ ጥላቻውን ስር ወደ ሰደደ ቅናት አሻግሮት እንደነበር ዘውዴ ረታ ጠቅሰዋል፡፡ ከዚህም አልፎ ተርፎ ነገረ ህልሙ በመኳንንቱ መካከል መከፋፈልና ሽኩቻ ስለፈጠረ ምንሊክ ሲሞቱ ባለሙሉ ስልጣን ሞግዚት የነበሩት ራስቢትወድ ተሰማ ናደው ሳይቃጠል በቅጠል ብለው በወጣቶቹ መሀል ሠላም እንዲሠፍን በሊቀጳጳስሱና በመኳንንቱ ፊት የሚከተለውን መሀላ አስፈጽመዋል፡-

1. ልጅ እያሱ ደጃች ተፈሪን ባላናጣ አድርገው በመመልከት ከሹመታቸውም ሆነ ከማዕረጋቸው እንዳይኳቸው / ምንም እንኮን ልጅ እያሱ ኋላ ቃላቸውን በልተው የሐረርጌ ሹመታቸውን ከተፈሪ ቢነጥቋቸውም/

2. ደጃች ተፈሪ በሚወራው ህልም የእምነት መንፈስ እንዳያድርባቸውና ለልጅ እያሱ ታዛዥነታቸውን እንዳያጐድሉ

ከዚህም በተጨማሪ በዘውዴ ረታ መጽሐፍ ውስጥ ብዙ ፍፃሜያቸው እንደፍቻቸው የሆኑ ህልሞችን እናገኛለን፡፡ ከነዚህም ውስጥ ንግስተ ነገስት ዘውዲቱ ከዘመነ ማርቆስ 1922 እና ራስ መኮንንም ከ1898 በህይወት እንደማያልፉ ግለሰቦቹ በህልማቸው ማየታቸውን ተጽፎ እናገኛለን፡፡

## 2. የሲግመንድ ፍሮይድ ''ኢጐ ዲፌንስ'' ንድፈ ሀሳብ

እንደ ቬናው ሊቅ ሲግመንድ ፍሮይድ እይታ ከሆነ የአንድ ሰው ስብእና የተሠራው ከሁለት ተቃራኒ የሚጋጩና አንድ አስታራቂ ከሆነ ክፍል ነው፡፡ የመጀመሪያው ክፍል ስንወለድ አብሮን የተወለደና ከእንስሳት ጋር አንድ የሚያደርገን የደመነብስ ክምችት ክፍል ነው፡፡ ይህንን ክፍል ፍሮይድ ''ኢድ'' ብሎ ይጠራዋል፡፡ እዚህ ውስጥ ያሉ ደመነብሶች ህፃኑ ለመኖር የሚያስፈልጉትን የመብላት፣ የመጠጣት፣ የመጸዳዳትና ሌሎች ፍላጎቶች የያዙ ናቸው፡፡ ሆኖም እርካታን ወዲያው የሚፈልጉና ትግስት አልባ ናቸው፡፡ ሆኖም ፍላጐቶች ወዲያው የማይሟሉ ከሆነ ህፃኑን ከመኖር ፍላጎት (life instincts) ራስን ወይም ሌላውን ወደማጥፋት ፍላጎት (death instincts) ይቀይራሉ፡፡ በዚህም ሰአት ለምሳሌ ልጁ የእናቱን ጡት ፈልጎ በሰአቱ ባያገኝ በማልቀስ እንዲረብሽ፣ ራሱን ከወለሉ ጋር እንዲያላትም ወይም እናቱን እንዲሳደብ አልያም እንዲነክስ ያደርጉታል፡፡ ሆኖም እነዚህን አጥፊ ባህሪያት ማሳየት ፍላጎቱን አዲያሟላ እንደማያስችሉ ሲረዳ እንድያውም ተጨማሪ ጡጫና ቁንጥጫ እንደሚያስከትሉ ሲረዳ ሌላኛው የስብእና ክፍል ከ2-3 አመት ባለው እድሜ ውስጥ ማደግ የጀምራል፡፡ ይህ ክፍል "ኢጐ" ይባላል፡፡ ይህም ክፍል ሰውየው ውስጥ የ "ኢድ" ፍላጎቶች ባለመሟላታቸው ሊፈጠር የሚችለውን ውጥረት እና ብስጭት (frustration) ለመቀነስ በተቃራኒው ደግሞ እነዚህ ፍላጎቶች ስርአትን ጥሰው ቢወጡ ሰውየው ላይ ከቤተሰብና ህብረተሰብ ሊደርስ የሚችለውን ጥቃት ለመከላከል የሚሰራ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪም የ"ኢድ" ተቃራኒ ሆኖ ከ 5 አመት እድሜ ጀምሮ የሚያድገው የህብረተሰቡን ሀይማኖታዊና ባህላዊ ህጎች አስርጾ በሰውየው ውስጥ ጠበቃ ሆኖ የሚያገለግለውን የ"ሱፐር ኢጐ" የጸጸት (የህሊና ወቀሳ) ቅጣት ለማርገብ የሚሰራ ነው፡፡ ይህንን ሚናውን ለመወጣት "ኢጐ" በዋናነት የሚጠቀመው ዲፌንስ መካኒዝም $ የተባሉትን መንገዶች ነው፡፡ ከላይ እንደተብራራው እነዚህ "ዲፌንስ መካኒዝሞች$ ሰውየውን ከብስጭት (frustration) ከውጫዊ ጥቃት ፣ (external threat) ና ከውስጣዊ የህሊና ጥቃት (guilt) ይከላከልለታል ፤ ሲከሰትም ይወጣዋል፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው የሰውን ሚስት በድብቅ ሊያማግጥ ይችላል፡፡ ሆኖም ማንም ሰው ባያየውም ቀንና ማታ የበደለኝነት /የጥፋተኝነት/ ስሜት ሊሰማው ይችላል፡፡ ሰውየው የሰው ሚስት እንዲያማግጥ ያነሳሳው ፍላጎት "ኢድ" ሲሆን፣ በሴትየዋ ባል ጥቃት እንዳይደርስበተት በድብቅ እንዲያደርግ ደግሞ ሃሳብ የሰጠው ክፍል #ኢጐ$ ነው፡፡ ሆኖም ማንም ስውየው ባያየውም የተማረውን አታመንዝር (የጎረቤትህን ሚስት አትመኝ) የሚለውን ቃል በመተላለፉ ምክንያት የህሊና ሰላሙንና መረጋጋቱን እንዲያጣ እንዲሁም በራሱ እንዲሸማቀቅ "ሱፐር ኢጐ" የተባለው ክፍል ያደርገዋል፡፡ በዚህን ሰዓት "ኢጐ$ ካሉት "ዲፌንስ መካኒዝሞች" አንዱን "ራሽናላይዜሽን" የተባለውን በመጠቀም እንኳን አንተ "ልብ አምላክ" የተባለው እንኳ ንጉስ ዳዊት ከወታደሩ ሚስት ጋር አመንዝሯል፡፡ በዚህም ሳያበቃ ኦሪዮ / የሴትዮዋን ባለቤት/ አስገድሎታል፡፡ እናም ተወው ባክህን ስው መሆን እራሱ መሳሳት ነው እያለ ከጸጸት ያወጣዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ አንዳንድ ምኞቶቻችን ደግሞ ህሊና ወይም ፈርሀ እግዚአብሄር የሚባለውን ክፍል ካሳደግን በኋላ ልንፈጽማቸው አይደለም ማሰባችንን እራሱ ይረብሸናል፡፡ በዚህ ወቅትም "ኢጐ" እነዚህ እንስሳዊ የ"ኢድ" ፍላጎቶችን ከሚያስተውለውና ከሚያገናዝበው የአይምሮአችን ክፍል (conscious Mind)በማስወጣት ፍላጎቶቻችንን ማስታወስ ከማንችልበት የአይምሮ ክፍል (Unconscious mind)ውስጥ ገፍትሮ ይጥላቸዋል፡፡ ይሄ "ዲፌንስ መካኒዝም" "ሪፕረሽን" ተብሎ ይጠራል፡፡ በጊዜ ሂደት መርሳታችንን ሁሉ እንረሳለን፡፡ ሆኖም እነዚህ የረሳናቸው እንስሳዊ ፍላጎቶች ከሰመጡበት የትዝታ ውቅያኖስ ውስጥ ሆነው ለመውጣትና ለመርካት መራር ትግል ያደርጋሉ፡፡ በዚህም ወቅት ሰውየው የስነልቦና ውጥረት ውስጥ ይገባል፡፡ እነዚህን አስፈሪና አደገኛ ፍላጎቶችን የሚፈጥሩት ውጥረት ለመቀነስ "ኢጐ"አዲስ "ዲፌንስ መካኒዝም"ይጠቀማል፡- ህልም (Dream)፡፡ ሆኖም ፍላጎቶች ከህልም በኋላም ታወሰው ሰውየውን ማለሙ የበለጠ ሊረብሸው ስለሚችል ህልሞቹ በማያስጨንቅ መልኩ (in disguised form) ይገለጣሉ፡፡

ለምሳሌ ከ ሲግመንድ ፍሮይድ የስብእና እድገት ንድፈ ሃሳብ ውስጥ አወዛጋቢ የሆነው "ኤዲፐስ ኮምፖሌክስ" ነው፡፡ ይሄ ሀሳብ (concept) የሚነግረን ነገር እያንዳንዱ ወንድ ልጅ ከ3-5/6 አመት ባለው ጊዜ እናቱን የማግባት (ማፍቀር) ስሜት እንዳለው እና አባቱን እንደባላንጣ የማየትና የማጥፋት ፍላጎት እነደአለው ነው፡፡ ሆኖም አባቴ ይህንን ስሜትን ካወቀብኝ ወሸላዬን ይቆርጥብኛል ብሎ ስለሚፈራ (Castration Anxiety)ከእናቱ በአካል መራቅ ይጀምራ፡፡ ሆኖም ልጁ የፍቅር ስሜቱን ማርከተት እንዲችል "ኤጐ" እንደ አባቱ እንዲዘንጥ፣ እንዲለብስ እና እንደንጎራደድ ያደርገዋል፡፡ በዚህም ወቅት ልጅ አባቱን በመምሰሉ እናቱን በፍቅር እንዳሳበዳት አድርጎ እንዲሰማው ያደርገዋል፡፡ ይሄ "ዲፌንስ መካኒዝም" ደግሞ "አይደንቲፊኬሽን$ ይባላል፡፡ ይህ ፍላጎት ግን በሚገባው ደረጃ በዚህ እድሜ ከልረካ ሰውየው የስነ-ልቦና ቀውስ (Psychological Disorder) እንዲገጥመው መሰረት ይጥላል፡፡ ይህንንም ለማቃለል ህልም ስራ ላይ መዋል ይጀምራል፡፡ ይህ እንዴት እንደሚሰራ ፍሮይድ መዝግቦ ካስቀመጣቸው የስነ ልቦና ታማሚዎች ህልም ውስጥ አንዱን እንይ፡ ታማሚው በአንድ ለሊት ከአንዲት ትዳር ካላት ሴት ጋር ድብቅ የፍቅር ግኙነት ሲያደርግ ያ"ያል፡፡ ሆኖም ገና ለገና ባሏ ያውቅብኛል ብሎ ስለፈራ ባሏን መንከባከብና ጥሩ ጓደኛ ሆኖ ሲቀርብ ያያል፡፡ ፍሮይድም ይህ ታማሚው ሊያማግጣት የሚፈልጋት ሴት እናቱ እንደሆነችና ጓደኛ የሚያደርገውም ባሏ አባቱ እንደሆነ ይፈታለታል፡፡ በፍሮይድ እይታ ይህ ሰው "የኤዲፐስ ኮምፐሌክስ"ችግሩን እንዳልፈታና የስነ ልቦና ቀውሱም መንስኤ ይኸው እንደሆነ ተዘግቦል፡፡

በዚህም ምክኒያት ፍሮይድ ወደሱ ይመጡ የነበሩ የስነልቦና ታማሚዎችን ቀውስ መንስኤዎች የተቀበሩት በ"አንኮንሺየንስ ማይንድ" ውስጥ እንደሆነና ወደ እነዚሁ አስፈሪና አደገኛ ምኞቶች መደረሻው ቅዱሱ መንገድ ህልም እንደሆነ ጽፏል ተጠቅሟልም፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ በፍሮይድ እይታ የህልም አላማ በህሊና (ፈርሃ እግዚአብሄር) ማደግ እና በገሃዱ አለም ክልከላ ምክኒያት ያላሳካናቸውን ምኞቶች ለማሳካት የምንጠቀምበት መንገድ ነው፡፡ ጥቅሙም እነዚህ ያልተሳኩ ምኞቶች የሚፈጥሩትን ውጥረት ለመቀነስ ነው፡፡ በተጨማሪም የስነልቦና ባለሞያዎች ለሚሰጡት ሙያዊ ድጋፍ (Psychotherapy) እንደ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡

የፍሮይድ የሙያ አጋርና ጓደኛ የነበረው ካርል ዩንግ በበኩሉ ህልም ካልተሳኩ የድሮ ፍላጎቶችን ከማርኪያም በላይ ነው ባይ ነው፡፡ በዩንግ እይታ ህልም ስለወደፊት ያልኖርንበት ዘመን የሚነግረን የመረጃ ምንጭ እንደሆነ ነው ፡፡ በዚህም ከ"ሱፐር ናቹራል" ንድፈ ሀሳብ አራማጆች ጋር ያመሳስላዋል፡፡ ለምሳሌ እራሱ ዩንግ የመጀመሪያው የአለም ጦርነት እንደሚነሳ ከአመት በፊት በህልሙ አይቶ ነበር፡፡

እነኚህ የ20ኛው ክፍለ ዘመን 2 ጥልቅ አሳቢያን የየእለት ህልማቸውን በመመዝገብ እና በመተርጎም ግኝታቸውን እራሳቸውንና በሽተኞቻቸውን ለመርዳትና ድጋፍ ለመስጠት ተጠቅመውበታል፡፡ ሆኖም ለየህልሙ የሚሰጡት ፍቺ ባላቸው የስብእና እድገት ንድፈ ሃሳብ መለያየት ምክኒያት የተለያየ ሆኗል፡፡ ይህም በአንድ በኩል በሚሰጡን የህልም ፍቺ ላይ እርግጠኛ እንዳንሆን ያደረገ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ለተጨማሪ ምርምር በር ከፋች ሆኗል፡፡

## 3. "ኒውሮ ባዮሎጂካል" ንድፈ ሀሳብ

ይህንን ንድፈ ሃሳብ የጻፉት ሆባሳንና ማከርሌ ሲሆኑ እንደነሱ እምነት ህልም የሚፈጠረው "ኮርቴክስ" (Cortex) የተባለው የአንጎል ክፍል በእንቅልፍ ሰዓት የሚደርሱትን ሞገዶች ትርጉም ለመስጠት በሚያደርገው ጥረት ነው፡፡ ሆኖም እንቅልፍ በሚወስደን ሰዓት በተለይም ፈጠን የአይን እቅስቃሴ እንቅልፍ (Rapid Eye Movement Sleep) የሚባለው የእንቅልፍ ደረጃ ላይ ስንደርስ መረጃ ከስሜት ህዋሳቶቻችን ወደ አንጎል አይደርስም (Input attenuation)፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አጥንቶቻችን አይታዘዙንም (Skeletal Paralysis)፡፡

በዚህ ወቅት "ፖንስ" የተባለው የታችኛው

የአንጎላችን ክፍል "ፒጂኦ" የተባሉ ሞገዶችን ይልካል፡፡ የእነዚህ ሞገዶች የሚላኩበት ዋና ምክንያት ፕሮቲኖች እንዲያዘጋጁ መልእክት ለማድረስ ነው፡፡ ሆኖም ሞገዶቹ በሚሰረጩ ወቅት የተለያዩ የአንጎል ስርዓቶችን የሚቆጣጠሩ ክፍሎችን ስለሚነኩ (ለምሳሌ

ስሜትን የሚቆጣጠረውን "ሊምቢክ

ሲስተም"፣ መረጃን የምናከማችበትን

"ሂፖክምፐስ") "ኮርቴክስ" እነዚህን ሞገዶች ከውጭ የገቡ መስሎት ከዚህ በፊት ካስቀመጥናቸው መረጃዎች ጋር በመደባለቅ በህልም ውስጥ የምናያቸውን ምስሎች፣ድምጾች፣እንቅስቃሴዎች እና ስሜቶች (ደስታ ወይም ሃዘን) ይፈጥራል፡፡ በዚህ ወቅት ህልም አየን እንላለን፡፡ ስለዚህ በዚህ ንድፈ ሃሳብ መሰረት ህልም

ማለት "ኮርቴክስ" ከአንጎል የሚለቀቁ ሞገዶችን ለመረዳት ሲል የሚፈጥረው ምስል፣ድምጽ፣ ስሜትና እንቅስቃሴ ብቻ ነው፡፡ በዚህም ምክኒያት ስር የሰደዱ የስነ ልቦና ችግሮችን መንስኤ የምናወቅበት አልያም የወደፊቱን እጣፈንታችንን ለማወቅ የሚያስችለን ግብዓት የለውም፡፡

ይህም ነጥብ "ኒውሮ ባዮሎጂካል" ንድፈ ሃሳብን ከመጀመሪያዎች ሁለት ንድፈ ሃሳቦች ይለዩታል፡፡

ከዚህ በታች አንዳንድ በሳይንስ የተረጋገጡና

ስለ ህልም የተጠቀሱ እውነታዎች ተዘርዝረዋል፡፡

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# ጥቂት ስለስነምግባር

## ክፍል ሁለት

ከአለባቸው አስፋው

## ብቁ የመንግስት ሠራተኛ መለያዎች

### 1. ሚ ስ ጢ ር

#### መጠበቅ

ሁሉም የመንግስት ሠራተኛ በየደረጃው ካለበት የሥራ መደብ ጋር ተያይዞ ተቋማዊና ተገልጋይን የሚመለከቱ መረጃዎችን በተለየ ሁኔታ የማወቅ ዕድል አለው:: መንግስት የመረጃ አያያዝን በተመለከተ ያወጣቸው ህጎች እንደተጠበቁ ሆኖ መረጃዎች ለሌላ ወገን ይፋ የሚደረጉበት ሁኔታ ተቋማዊ ማዕቀፍ ሊኖረው የሚገባ ነው:: ለምሳሌ ወደኛ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡ ተገልጋዮች ወደግቢ ከሚገቡበት ጀምሮ ልዩ ልዩ ጉዳዮቻቸውን ጨርሰው እስኪወጡ ባለው ሂደት ራሳቸውን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለተለያዩ ክፍሎች ይሰጣሉ:: ይህ በስራ ምክንያት ወደእጁ የገባ የዩኒቨርሲቲው ሠራተኛ ያለአግባብ የተገልጋዩን መረጃ እንዲበትን አይጠበቅም፤ አይገባምም:: ይህ ማለት ግን የመንግስት ሠራተኛው እንደዜጋ በህገ መንግስቱ የተረጋገጠለትን የመናገርና ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት መገደብ ማለት ሊሆን አይችልም::

### 2. ስጦታን በተመለከተ

የመንግስት ሠራተኛ ማናቸውንም ያለበትን ተቋም አገልግሎት ያለክፍያና ውድ ዋጋ ያለው ስጦታ መፈጸም ይጠበቅበታል:: ተገልጋዮች ከአገልግሎት አሰጣጥ አኳያ ለማመስገን ወይም ቀጣይ ግንኙነትን ለማሻሻል ወይም በስጦታቸው አማካኝነት ውሳኔዎች ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ሲሉ ስጦታዎችን ሊያቀርቡ ይችላሉ:: ሆኖም የመንግስት ሠራተኛው ይህን መሰል ስጦታ በተቀበለ ቁጥር ሃቀኝነቱን አደጋ ላይ እየጣለ መሄዱ የማይቀር ነው:: በመሆኑም ስጦታን ዝም ብሎ መቀበል በመንግስት ተቋማት ውስጥ ተቀባይነት አይኖረውም:: የመንግስት ሠራተኛ ሁሌም ቢሆን በሥራ ነፃነቱ ላይ መደራደር ስለማይኖርበት በስጦታ አጥር ውስጥ ራሱን አስገብቶ መገኘት አይጠበቅበትም::

### 3. የጥቅም ግጭትን ማስወገድ

የመንግስት ሠራተኛ እንደማንኛውም ዜጋ የራሱ፣ የቤተዘመዱ፣ የጓደኞቹ . . . ወዘተ የግል ሥራዎች ጋር ግንኙነት ይኖረዋል:: ሃቀኝነት ላይ የተመሰረተ የዜጎችን ጥቅም የማይጎዳ ተግባር ማከናወን የሚችለው በመንግስት ሥራ ኃላፊነቱ የሚያከናውነው ተግባር ከግል ፍላጎቱ በሚመነጭ ግፊት ያልተመራ እንደሆነ ብቻ ነው:: በመሆኑም በሚሰራውና በሚወስነው ስራ አንፃር ወደግል ፍልጎቱ የሚጎትተው ነገር አለመኖሩን ማረጋገጥ አለበት:: በመሆኑም በመንግስት ስራ ላይ ሊሰማራ የሚከለከሉ የግል ሥራ ስምሪቶች ካሉ ማጥራትና ማወቅ ግዴታው ነው:: ይህም ሆኖ የዕለት ከዕለት ሥራው ባልታሰበ ሁኔታ ከራሱ የግል ጥቅም ጋር ሊያያዝበት ይችላል:: ይህ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ የተዛባ ውሳኔ እንዲሰጥ ያሉትን አማራጮች ሁሉ መፈተሽ ይገባዋል:: ለምሳሌ ቅጥር ወይም የደረጃ እድገት ሲፈጽም የራሱ ቤተሰብ አባል ተወዳዳሪ ሆኖ ቢገኝ ጉዳዩን ግልጽ በማድረግ ራሱን ከሂደቱ ማግለል አለበት:: የመንግስት ግዥ ውድድር የቤተዘመድ ድርጅት ተወዳዳሪ ሆኖ ቢገኝም ጉዳዩን በተመሳሳይ ግልጽ አድርጎ ራሱን ከዚህ ሂደት ማውጣት የተሻለ አማራጭ መሆኑን ማጤን ይገባል:: በአገራችን ትልቁ የአገልግሎትና ዕቃ ገዥ መንግስት በመሆኑ የመንግስት ሠራተኞች አብዛኛው ሥራቸው በተለያየ መልክ ቢሆንም ከግዥ ሥራ ጋር የተያያዘ ነው:: በመሆኑም የመንግስት ሠራተኛው ሥራውን በፍጹም ነፃነት ለመወጣት ያስችለው ዘንድ ራሱን ከድለላና ስጦታ ቃሎች ነፃ ሆነው ተግባራቸውን በግልጽነት፣ በኃላፊነትና በተጠያቂነት መንፈስ ማከናወን ይጠበቅባቸዋል::

### 4. የመንግስት ሃብትና ንብረት አጠቃቀም

የመንግስት ሠራተኛ ከጥቂት ብሮች ጀምሮ በሚሊዮን እስከሚቆጠር የህዝብ ሃብት በእጁ በአደራ የሚያስተዳድር የህዝብ ታማኝ አልጋይ ነው:: የመንግስት ሠራተኛ ጊዜ በእጁ ነው፣ የተመደበበትን ኃላፊነት ለመወጣት ይችላል፣ ሊያባክነውም ይችላል:: በንብረት ላይ ያዛል፣ ገንዘብ ይከፍላል፤፣ ይቀበላል፣ ሌሎች እንዲከፍሉም ያዛል/ ምህረትም ይሰጣል፤: ፋክሱ፣ ኮምፒዩተሩ፣ ፕሪንተሩ፣ ወረቀቱ፣ ኤሌክትሪኩ፣ ስልኩ፣ መኪናው እንደስራ ባህሪው በእሱ/ሷ እጅ ይገኛል:: የሥራ ሰዓቱን ለግል ስራው ማዋል ይችላል:: ሃብቱን በሙሉ እንዲያስተዳድር ዕምነት የተጣለበትን የመንግስት ሠራተኛ ነው:: እምነቱን ለመወጣትም የቄሳርን ለቄሳር ነውና የመንግስት ሃብት ለታለመለት ዓላማ ብቻ እንዲውል በማድረግ አደራውን መወጣት አለበት:: ከዚህ አልፎም ሌሎች የመንግስት ሃብት ለግል ጥቅማቸው ለማዋል የሚዳዱ ግለሰቦችን ወደትክክለኛ አስተሳሰብ እንዲመጡ መጣር ይጠበቅባቸዋል::

### 5. ኢ-ሜይልና ለሌሎች የቢሮ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም

ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች በተለይ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወሳኝ መገልገያዎች ናቸው:: ይሁን እንጂ እነዚህ ቴክኖሎጂዎች ዕውን ስራን ለማሳለጥ አለም ወደደረሰበት ብልጽግና እንድንደርስ ዘንድ እያገዙን ነው ወይንስ ተስፋ የሚጣልባቸው ዜጎቻችንነ እያመከኑብን ይሆን ብሎ ራስን መጠየቅ ይገባል:: በድረ-ገጽ የሚለቀቁ እልፍ አዕላፍ መረጃዎች ራስን ባለመግዛት ምክንያት አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳያደርሱ መጠንቀቅን ይሻሉ:: የመንግስት ሠራተኛው ቴክኖሎጂን የመጠቀም አቅሙ መዳበር ያለበት ሲሆን ለዚህ ደግሞ ዋነኛው ተዋናይ ራሱ ነው:: ይህ እንዳለ ሆኖ የቴክኖሎጂ ዕውቀትን ተገልጋዩን በበለጠ ፍጥነት፣ ጥራትና ውጤታማነት እንድናገለግለው እንጂ አልባሌ ድረ-ገጾች ላይ አፍጠን ተገልጋዩን ለምሬት የምንዳርግበት ሊሆን አይገባም:: ከዚህ በተጨማሪ የመንግስት ሠራተኞች በስራ ቦታቸው ላይ ሆነው ወሲብን፣ ዘረኝነትን ጥላቻን የሚሰብኩ ስድብንና የሌሎች ስብዕናን የሚነኩ መረጃ እንዳይለዋወጡ፣ የምስልና ድምጽ ቀረፃዎችን እንዳያከማቹና እንዳያሰራጩ የአገሪቱ ህግ መድንገጉን መገንዘብ ይኖርባቸዋል:: ትክክለኛ የመንግስት ሠራተኛ ከሆኑም ሞራላቸው ይህን አይፈቅድላቸውም::

# ቁንጠኛው

ከገጽ 10 የዞረ...

ቆሜአለሁ ከበርሽ ማዶ ...››

ቤቲ ትዕግስትንና ሳምሪን አስከትላ እነ ቁንጠኛው ካሉበት ጭፈራ ቤት ውስጥ ገባች:: አስተናጋጆቹም ተቀብለው ቦታ ሰጡአቸው በነ ኤርሚያስ ትይዩ፤
‹‹ጋይስ ግቢ እንገባለን ወይስ ውጭ ነው እምናድረው?›› ሲል አስመላሽ ጥያቄ አቀረበ::
‹‹እንደ አየሩ ፀባይ:: ከተመቸንና ከተመቻቸን እናድራለን:: በተቃራኒው ከሆነ ደግሞ ወደ ግቢ እንነካዋለን:: አይመስላችሁም?›› አለ ቁንጠኛው::
‹‹ምርጥ ሃሳብ:: ሳቢው ከበቃን አሪፍ ነው::›› ኤርሚያስ መለሰ::
‹‹እሱ እንኳን በቂ ይመስለኛል:: ነገር ግን ‹‹ፈርኃን›› የምንልበት የለንም:: ›› አስመላሽ መለሰ::
‹‹ለዛ ጣጣ የለውም አዩ ያበድረናል:: ባይሆን አሁን ሳብ ሳብ እያደረጋችሁ: : ... ፊት ለፊታችን ያሉትን ችኮች አያችኋቸው?›› አለ ቁንጠኛው ወደነ ትዕግስት እያፈጠጠ::
‹‹እሽ ባለፈው ‹‹ቪድዮ›› ላይ ዶርም ውስጥ እራቁታቸውን ሁነው ሲጨፍሩና ሲሳሳሙ የነበሩት ናቸው አይደል?›› አለ ኤርሚያስ::
‹‹ሌዝቢያኖች ሳይሆኑ አይቀሩም:: አሁን እኮ በየ ቦታው ተበራክተዋል: :›› አለ አስመላሽ::
‹‹አይመስለኝም:: እንዳውም ሱሴዎች ሳይሆኑ አይቀሩም::›› ቁንጠኛው መለሰ::
‹‹አየህ እንዴት እንደሚያፈጡ: : በእርግጠኛነት ስለ እኛ ነው የሚያወሩት::›› አለና ኤርሚያስ በግራ እጁ የቁንጠኛውን ትከሻ መታ መታ አደረገው:: ትዕግስትና ቤቲ በነቁንጠኛው ፊት ለፊት ትይዩ ቆመው፤ ሳምሪ ደግሞ ጀርባዋን ሰጥታ ያወራሉ::
‹‹እንዴታባቱ ነው የሚያፈጠው በማሚ!›› አለች ቤቲ ቁንጠኛውን እያየች:: ‹‹ሲያምራችሁ ይቀር በሉልኝ:: ምድረ ድሃ ሁሉ::›› አለች ሳምሪ ዙራ ሳትመለከት::
‹‹እባክሽን ሳምሪ እንደዛ አትበይ:: ሁላችንም እንደዛ አይደለን እንዴ? ኢትዮጵያ ውስጥ እኮ ነው ያለነው: : ባይሆን በዲቪ ከተገላገልናት በኋላ ብናወራ ይሻላል::›› አለች ትዕግስት አንዴ ሳምሪን አንዴ ደግሞ ቤቲን እየተመለከተች::
‹‹ኢትዮጵያን ውስጥ ብንሆንም ሁላችንም ድሆች አይደለንም:: አንዳችን ለአንዳችን የተሻልን ስለሆንን::›› አለች ሳምሪ ቢራዋን እየተጎነጨች::
‹‹በነገራችን ላይ ያ ማሃል ላይ ያለውን ልጅ አይችሁት? አንዴ ባህል ማዕከል ላይ ሳየው አድንቄው ልሞት::›› አለች ትዕግስት ቁንጠኛው ላይ እያፈጠጠች፤ ሳምሪም አንዴ ዞር ብላ መልከት ካለች በኋላ ‹‹ይሄ ቀጫጫው?›› አለች::
‹‹ቅጥነቱን ሳይሆን ጥበቡን ብታይ ወይኔ እንዴታባቱ እንደሚያሳብድ! የተሰጠኦ ሰው ነው:: ይገጥማል፣ ይተውናል፣ ይስላል:: በተለይ ደግሞ ሲዘፍን ነፍስሽ ወደሰማይ ሰማያት ተነጥቃ ትሄዳለች::››
‹‹ቲጅዬ ግን ሰላም ነሽ?›› አለች ቤቲ በግርምት አይን እያየቻት::
‹‹አምና! ምን ነው?››
‹‹አይ በጣም አካብድሽለት ብዬ ነው::››
‹‹ግድ የለሽም አንዴ ስታይው ካወራሁለት በለይ ታወሪለታለሽ::››
‹‹እና ያለ ና ::›› አለች ቤቲ ያስቀመጠችውን ቢራ ወደ ከንፈሯ እያስጠጋች::
እነቁንጠኛው ሳይታወቃቸው ብዙ ቢራ ስለደጋገሙ የየራሳቸውን መለየት አቅቷቸዋል::
‹‹ተው ባክህ ይሄኛው ነው የኔ::›› ኤርሚያስ::
‹‹የኔው መች ጠጣሁትና ይሄ እኮ ያለቀ ነው::›› አስመላሽ::
‹‹ጋይስ ኪራይ ሰብሳቢዎች አትሁኑአ:: የየራሳችንን እንጠጣ::›› ቁንጠኛው::
‹‹መጨፈር አማረኝ::›› አለ አስመላሽ::
‹‹ለምን ችኮቹን አናስጨፍራቸውም?›› ቁንጠኛው ሃሳቡን አቀረበ:: ከመቀመጫ ተነስቶ ሲሄድ ኤርሚያስና አስመላሽም ተከትለውት ሄዱ:: እነ ትዕግስት ጋ ሄደው ለብቻቸው ሲጨፍሩ ከቆዩ በኋላ ንክኪ ሲየበዙ እንዲግባቡ እድሉን አመቻቸላቸው:: ቀስ በቀስ ሶስቱም ጥንድ ሆነው ጨዋታውን እንዲደራ አደረጉት: : መነካካቱ፣ መተሻሸቱ፣ መሾካሾኩ ... ቀጠለ::

**ይቀጥላል::**

ማስተዋሻነቱ ስእነ ሰለሞንዎች::

በአረጋዊ ሰለሞን (3ኛ ዓመት የጋዜጠኝነት እና ተግባቦት ተማሪ) 0918311934

## ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን

የናይል ጋዜጣን ተነባቢነት ለማሳደግ የዝግጅት ክፍሉ የተለያዩ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡ እርስዎም አስተማሪ እና አዝናኝ የሆኑ የተለያዩ ጹሁፎች፣ ማህበራዊና ሳይንሳዊ ነክ ጉዳዮች፣ የካርቱን ስእሎች፣ ቀልድ ፣ ግጥም እና የመሳሰሉትን ጥበብ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር G502E በሚገኘው ቢሯችን ድረስ በመምጣት ወይም በኢሜል gracetsegi@gmail.com ይላኩልን፡፡

በናይል ጋዜጣ በቀጣይም ለእናንተ ይመጥናሉ ያልናቸውን የተለያዩ ጽሁፎች ማቅረብ እንደምንቀጥል እየገለጽን ለቀጣዩ የጥቅምት ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ በአድራሻችን መላክ ወይም በኢሜል አታች ማድረግ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡

ዝግጅት ክፍሉ

# Dealing with Sexual Problems and Abnormalities: Why do people experience sexual dysfunctions?

***Kibrom Mengistu Feleke (Psychology Department, FEBS)***

Sexual functioning is an essential aspect of human existence that can be a very rewarding or upsetting part of a person's life. Sexuality involves such a driving force in human nature, and is such an emotionally charged phenomenon, that it is not surprising that there are problems associated with this facet of human behavior.

We live in a culture that idealizes and exaggerates the idea that sex should be spontaneous, perfect, or great every time. Yet, it is normal to have sexual difficulties. Almost every person at some point in his/her life will experience some form of sexual problem or dysfunction, important enough to want to talk with his therapist or doctor. Yet only 23% of men reported that they did in fact discuss their concerns with a professional clinician. Dealing with sexual problems is, therefore, almost a universal experience for both men as well as women. Obviously, these problems can subvert sexual health. Hence, this article aims to briefly describe some common sexual problems and their causal factors by providing a more scientific basis for understanding sexual problems.

### *What Is Abnormal Sexual Behavior?*

*What is abnormal sexual behavior for you? What criteria do you use in labeling sexual behaviors as 'abnormal'?* In general, the distinction between normality and abnormality in the sexual domain of behavior is complicated and far from clear. For this reading, however, sexual behavior is considered psychological disorder or abnormal if (1) it causes harm to other people, or (2) it causes an individual to experience persistent or recurrent distress or impairment in important areas of functioning. According to the first criterion, sexual molestation of a child is clearly a psychological disorder. For the second, a distressing, ongoing aversion to sexuality is a disorder.

One of the most commonly occurring sexual disorders both in men and women is what is called *sexual dysfunction*. Sexual dysfunctions involve conditions in which there is abnormality in an individual's sexual responsiveness and reactions.

Sexual dysfunctions are defined by the individual, often in terms of an intimate relationship and almost invariably in the context of cultural expectations and values about what constitutes normal sexual functioning. There is no one 'correct' pattern of sexual activity; what one considers dysfunctional, another may regard as healthy and normal. Unfortunately, people may regard themselves as having a sexual dysfunction without being aware of the extent to which their behavior falls within the range of normal behavior. An important factor to keep in mind about sexual dysfunction is, however, whether or not person feels distressed about the behavior.

In order to understand sexual dysfunction, it is necessary to understand human sexual response cycle. Accordingly, there are four phases of the sexual response cycle: *arousal, plateau, orgasm,* and *resolution*. During *arousal stage*, the individual's sexual interest heightens, and the body prepares for sexual intercourse (vaginal lubrication in the female, penile erection in the male). Sexual excitement continues to build during the *plateau phase*, and during the *orgasm phase*, the individual experiences muscular contractions in the genital area that are associated with intense sensations of pleasure. The *resolution phase* is a period of return to a physiologically normal state. People differ in their typical patterns of sexual activity, in that some people progress more readily through the phases and others progress at a slower pace. Not every sexual encounter necessarily involves all phases, either.

Sexual dysfunctions are associated with the *arousal* and *orgasm phases*, as well as with *a person's overall level of sexual desire*. Some people with sexual dysfunctions have little or no interest in sex; others experience a delay in any phase of sexual arousal or do not become aroused at all. Others may become highly aroused but are unable to experience the sexual release of orgasm. Still other people proceed too rapidly through the phases from arousal to orgasm and, therefore, feel that sexual relations lack the emotional meaning associated with a more relaxed approach. In some cases, one's partner may feel distressed over what seems like unacceptable deviations from desired pattern of activity. Yet, other sexual dysfunctions are the result of the experience of pain rather than pleasure during a sexual encounter.

The most common sexual dysfunctions include premature ejaculation, erectile dysfunction, inhibited sexual desire, orgasmic disorder, ejaculatory inhibition, sexual pain disorders, compulsive masturbation (often to porn Web sites), and a sexual secret (variant arousal pattern, preferring masturbation over couple sex, history of sexual trauma, and sexual orientation conflicts).

### Characteristics and Causes of Sexual Dysfunctions

Professionals debate whether sexual problems should be considered medical, psychological, or relational problems. Clinicians refer to several distinctions in characterizing the nature of a sexual dysfunction. First, they question whether a dysfunction is attributable to psychological factor, such as depression or relationship problems, or is due to a combination of psychological factors and physical factors, such as illness or substance use. They also distinguish between lifelong and acquired types, as well as between situational and generalized sexual dysfunctions. A *lifelong dysfunction* has been present since the beginning of active sexual functioning, whereas *acquired problem* has developed following a period of normal functioning. *Situational dysfunctions* occur with only certain types of sexual stimulation, situations, or partners, whereas *generalized dysfunctions* are not limited.

The reality is that sexual problems are multi-causal and multidimensional. Hence, sexual dysfunctions can be caused by psychological problems, physical/medical problems, or their interaction. The psychological factors leading sexual dysfunction most commonly involve negative attitudes towards sex, traumatic or stressful experiences or conflicts with sexual partners. A number of factors, including medical illness, side effects of drugs, nervous system injury and hormonal deficiencies can cause sexual dysfunctions. Medical illness (such as diabetes, blood pressure, heart disease, cancer) does not stop sexual function, but it usually does alter it.

One feature of sexual dysfunctions is that sometimes, sexual dysfunctions are signs or symptoms of problems in a person's life that do not directly pertain to sexuality. For example, a person who is very upset about job-related stresses or family problems may develop sexual performance problems. At times, people are not even aware of the connection between the sexual problem and other life stresses; and, of course, some sexual problems are more clearly connected than others to problems within a particular relationship or to experiences in the person's past in which the foundation of a sexual problem was established.

You may wonder where to draw the line between ordinary variations in human sexual responsiveness and the pattern of psychological disorder represented by a sexual dysfunction. Sexual dysfunctions involve persistent and recurrent symptoms. To illustrate this point, consider two examples. Some months after the birth of her second child, Yeshi finds that she cannot regain her former interest in having sexual relations with her husband. At her sister's advice, Yeshi and her husband take a week vacation during which Yeshi's sister will care for the baby and older children. Although she still experiences occasional fatigue that dulls her sexual appetite, Yeshi regains her previous interest in sexual activity. This is because she does not have a disorder because her symptoms are temporary and non-recurrent. Treatment would not necessarily be indicated, other than her sister's commonsense advice.

In contrast to Yeshi's situation, the condition of Tadelech's desire for sexual relations with her husband has dwindled for the past 2 years, until it is now very infrequent. Tadelech eventually seeks treatment when she realizes that, unless things change, her husband might give up on her and look for sexual gratification outside the wedlock. Tadelech's loss of sexual desire has been persistent and is considered dysfunctional.

It is important to realize that, at times, other psychological problems are the basis of sexual difficulties. For example, abnormally low sexual desire in someone who is depressed would not be considered grounds for diagnosing a sexual dysfunction but, instead, would be regarded as part of the depression.

Many people with sexual dysfunctions, and even some professionals treating them, are quick to conclude that all sexual problems must be emotionally caused; they fail to consider that a sexual problem may be associated with physical illness, medication, or general level of health. For example, diabetes is a medical condition that affects millions of people in the world and is known to cause sexual dysfunction, particularly erectile problems in men. Without an understanding of this connection and comprehensive medical assessment, clinician could draw erroneous conclusion that a man's sexual problem is due to emotional or interpersonal causes.

Moreover, sexual problems can begin fairly innocuously but then develop into something more serious because of anxiety about the problem. For example, Kebede, who is preoccupied with work problems, experiences difficulty one night in getting an

continued on page 12




Talented students on STEM training



Novice female graduate assistants on training



የኢትዮጵያ ስታስቲክስ ማህበር ከዩኒቨርሲቲው ጋር የመግባቢያ ስምምነት ሲፈራረም




በሆሳዕና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ